በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ

ትምህርት ሚኒስቴር
2012 ዓ.ም

# መቅድም

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ህፃናት ጥራት ያለው ትምህርት ያለአንዳች የዘር፣ የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የኢኮኖሚ ደረጃ ወይም መልካ ምድራዊ ልዮነት በእኩልነት ለማዳረስ ያለው ቁርጠኝነት በበርካታ የሃገሪቱ መንግስታዊ ሰነዶች ተንጸባርቋል። በተለይም ባለፉት ዘመናት መሰረታዊ፣ የሰብአዊና የማህበራዊ መብቶቻቸውን ለተነፈጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጠው ልዩ ትኩረት ከፍተኛ ነው።

በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማቱ ዘርፍ ዝቅተኛ ተጠቃሚ ለነበሩ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች መንግስት ልዩ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው በሀገሪቱ ህገ-መንግስት አንቀፅ 89/4 ላይ በግልፅ ደንግጓል። በተጨማሪም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው አንቀፅ 3.7.7 በጉልህ እንዳስቀመጠው በትምህርት ዝግጅት፣ በስርጭትና በትምህርት ድጋፍ ግብዓቶች አጠቃቀም በቂ እድል ላላገኙ ሴቶች እና ህፃናት ልዩ አትኩሮት እንደሚሰጥ አረጋግጧል። እነዚህንም ለመተግበር ይቻል ዘንድ ትምህርት ሚኒስቴር አባል የሆነበትና ለታዳጊ ክልሎች የማበረታቻ ድጋፍ የሚሰጥ የፌደራል ልዩ ድጋፍ ቦርድ በሚንስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 128/2006 እንዲቋቋም ተድርጓል።

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት አገራችን በትምህርት ዘርፍ አመርቂ ስኬቶችን አስመዝግባለች። ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስም ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማትን በመገንባት የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ ስኬታማ እንዲሆን በመትጋት ላይ ትገኛለች። ለትምህርት ዘርፉ የዋለው መዋዕለ ንዋይ ካስመዘገባቸው አመርቂ ውጤቶች መካከል በትምህርት ሰርዓቱ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት የትምህርት ተሳትፎ መሻሻል፣ በከተማና በገጠር እንዲሁም በጾታ መካከል ያለው ልዩነት መጥበብ እና የታዳጊ ክልሎች የትምህርት ተደራሽነት መሻሻል ዋናዋናዎቹ ናቸው።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የትምህርት የልማት ግቦች ካሳኩ ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት መካካል አንዷ መሆን የቻለች ሲሆን አሁን ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ስራ ጀምራለች።

የአርብቶ አደር ትምህርት ጉዳይ ከሶስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ ከ1998 ዓ ም – 2002 ዓ ም ጀምሮ ልዩ ትኩረት ያገኘ ሲሆን ከ2000 ዓ ም ጀምሮ የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ በመሆኑ በርካታ ስኬቶች ተመዝግበዋል። ይሁን እንጂ ከአስር ዓመታት ትግበራ በኋላ ስትራቴጂው የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ የትምህርት ፍላጎቶች ይበልጥ ያረካ ዘንድ መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር ከብሪቲሽ ካውንስል (QESSP) እና ከዩኒሴፍ (UNICEF) በተገኘ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂን አሻሽሏል። በስትራቴጂው ውስጥ የተካተቱት የትምህርት አሰጣጥ ስልቶች በጣም ጠቃሚ እንደሚሆኑና በአግባቡ ከተተገበሩ የሚፈለገውን ውጤት እንደሚያስገኙና በዘርፉ የተቀመጠውን ራዕይ እውን እንደሚያደርጉ እምነቴ የጸና ነው። ስለዚህ የተሻሻለውን የትምህርት ስትራቴጂ እውን በማድረግ የአርብቶ አደሩ ማህረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን ሁሉም የዘርፉ ተዋንያንና አጋሮች የየበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪዬን አቀርባሁ።

በመጨረሻም የ2000 ዓ.ም የአርብቶ አደር ማህበረሰብ የትምህርት ስትራቴጂ በማሻሻልና የ2012 ዓ.ም ስትራቴጂን በማዘጋጀት የበኩላቸውን ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሁሉ ከፍተኛ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።

# ይዘት ማውጫ

ክፍል አንድ አጠቃላይ ጉዳዮች ........ 1
1.1. ስያሜ ........ 1
1.2. መግቢያ ........ 1
1.3. የቃላት ፍቺ ........ 3
1.4. የአርብቶ አደር ትምህርት ነባራዊ ሁኔታዎች /Situation Analysis/ ........ 4
1.4.1. የፖሊሲ ማዕቀፍ ........ 5
1.4.2. የአርብቶ አደር ትምህርት አሁን የሚገኝበት ሁኔታ ........ 6
1.4.3. የስትራቴጂው አፈጻጸም ........ 8
1.4.4. የአርብቶ አደር ትምህርት ትንተና ጥናት ........ 8
1.4. አርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ አስፈላጊነት ........ 8
1.5. ራዕይ፣ ዓላማ እና መርሆዎች ........ 8
1.5.1. የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ዓላማ ........ 9
1.5.2. የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ መርሆዎች ........ 10
ክፍል ሁለት፡ ስትራተጂዊ ተግባራት ........ 11
2.1. የአርብቶ አደር ትምህርት የአቅርቦት ስልቶች ........ 11
2.1.1. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ስልቶች ........ 11
ለ.የተፋጠነ የህፃናት ትምህርት ዝግጁነት (ASRP)፡- ........ 13
2.1.2. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የአፈጻጸም ስልት ........ 14
2.1.3. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የአቅርቦት ስልት ........ 15
ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡- ........ 15
i. መደበኛ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ........ 15
ii. አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ........ 17
iii. የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ........ 22
2.1.4. ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ........ 25
i. መደበኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 26
ii. የከፊል አዳሪ ትምህርት ቤት ........ 27
iii. ሆስቴሎች ........ 29
2.1.5. የርቀት ትምህርት ........ 31
2.1.6. የተቀናጀ ተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት ........ 32

ክፍል ሦስት ፡ ዘርፈ-ብዙ ስትራቴጂያዊ ተግባራት ........ 36
3.1. የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ........ 36
3.2. የአርብቶ አደር ልጃገረዶች ትምህርት ........ 39
3.3. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ........ 40
3.4. የአደጋ ጊዜ ትምህርት ........ 41
3.5. የትምህርት አመራርና አስተዳደር አቅም ግንባታ ........ 42
3.6. የፋይናንስ አሰባሰብና አጠቃቀም ........ 43
3.7. የአጋርነት ስራ ለትምህርት ልማት ........ 44
3.8. የተማሪዎች የምዘና ሥርዓት ........ 47
ክፍል አራት፡ ስትራቴጅያዊ ተግባራትና የፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ........ 48
4.1. ስትራቴጅያዊ ተግባራት ........ 48
4.2. የፈጸሚና የአጋር አካላት ተግባርና ሃላፊነት ........ 49
4.2.1. ትምህርት ሚኒስቴር ........ 49
4.2.2. የክልል ትምህርት ቢሮዎች ........ 50
4.2.3. የዞን ትምህርት መምሪያዎች ........ 52
4.2.4. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ........ 53
4.2.5. የጉድኝት ማዕከላት ........ 54
4.2.6. ትምህርት ቤቶች /ጣቢያዎች/ ........ 54
4.2.7. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ........ 55
4.2.8. የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ........ 56
4.2.9. ከአጋር ድርጅቶች የሚጠበቁ ተግባራት ........ 57
ክፍል አምስት ........ 58
ክትትል፣ ግምገማ እና የትምህርት መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ሥርዓት ........ 58
5.1. የክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 58
5.2. የትምህርት መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ስርዓት ........ 60

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ጉዳዮች

### 1.1. ስያሜ

ይህ ስትራቴጂ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ቁጥር---/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 1.2. መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት ጥራት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ዜጎች ያለምንም የዘር፣ የሃይማኖት፣ የመልከዓ ምድር ልዩነት በእኩልነት ለማዳረስ በትጋት እየሰራ ይገኛል። የጆሚቲየን (Jomitien 1990) እና የዳካር (Dakar 2000) ትምህርት ለሁሉም ጉባኤዎችን እንዲሁም የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦችና የዘላቂ የልማት ግቦችን ተቀብሎ በመተግበር ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ አርብቶ አደር ህዝብ ብዛት በግምት ከ12-15 ሚሊዮን የሚደርስ ሲሆን ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የቆዳ ስፋት ከ60-65 በመቶ በሚሆን ቦታ ላይ ሰፍሮ ይገኛል። በቀደሙት መንግስታት የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ትምህርትና ጤናን ለመሳሰሉት ማህበራዊ አገልግሎቶች የነበረው ተደራሽነት በጣም ውሱን ነበር። ከሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች አንፃር ሲታይ በእነዚህ አካባቢዎች የነበሩት መሰረተ ልማቶች ፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶችና የመገናኛ አውታሮች ልማት ደካማ ነበር። የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ችግሮች ከሌላው የገጠር ማህበረሰብ ችግሮች ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የተለየ የሚያደርገው ግን እጅጉን የተገለለና የተገፋ ህብረተሰብ ስለነበረ ነው። በነዚህ አካባቢዎች የሚታየው የምግብ እጥረት ፣ ደካማ የማህበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦትና የአቅም ግንባታ ተቋማት እጥረት ለአመታት የዘለቁ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መገለል ውጤቶች ናቸው።

በ1986ቱ ብሄራዊ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በተሰጠው ትኩረትና ልዩ ድጋፍ መሰረት ለአርብቶ አደሩ የሚሰጠው የትምህርት አገልግሎት መሻሻልን አሳይቷል። በዚህ ፖሊሲ ጥላ ስር ከሶስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ ጀምሮ የአርብቶ አደር ትምህርት ተገቢውን ትኩረት አግኝቷል። በ2000 ዓ.ም በተዘጋጀው የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ የአርብ

አደር ማህበረሰቦች ያሉባቸውን ተግዳሮቶችና ያሏቸውን መልካም እድሎች ታሳቢ በማድረግ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለማዳረስ የተሻሉ ስልቶችን ለይቶ አስቀምጧል።

በመሆኑም የትምህርት አቅርቦቱን ከማስፋፋት አኳያ እጅግ አመርቂ ውጤት ቢመዘገብም በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለው የትምህርት ተሳትፎ አሁንም ከሀገራዊ አማካይ ተሳትፎ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው። እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ እጅግ በርካታ ህፃናት አሁንም ከትምህርት ውጪ ሲሆኑ በትምህርት ላይ ካሉትም በርካታዎቹ ትምህርታቸውን አያጠናቅቁም። ይህም በአርብቶ አደር ማህበረሰብና በሌላው ማህበረሰብ መካከል ያለውን ስር የሰደደ የትምህርት ልማት ልዩነት በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን ዘላቂ የልማት ግቦችንም ሆነ የሀገራችንን በ2025 እ.አ.አ የዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ የመሰለፍ የረጅም ጊዜ አገራዊ ራዕይ ስኬትን የሚያስተጓጉል ነው።

በአርብቶ አደር ማህበረሰብ አካባቢ በተፈጠሩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦችና ከ2000 ዓ.ም የአርብቶ አደር የትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ ልምድ ላይ በመመስረት ትምህርት ሚኒስቴር ስትራቴጂውን በ2012 ዓ.ም አሻሽሏል። በዚህ መሰረት የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂውን በይበልጥ ለማጠናከርና አርብቶ አደሩ አሁን የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ባካተተ መልኩና በውጤታማነት መፈጸም ይቻል ዘንድ አዳዲስ የተፈጠሩ የትምህርት ማቅረቢያ እድሎችን ለመጠቀም ሲባል ነባሩ ስትራቴጂን መከለስ አስፈልጓል ።
የ2012 ዓ.ም የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑትን እጅግ በርካታ የአርብቶ አደር ልጆችን ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችሉ ቁልፍ መርሃ ግብሮችንና ሰልችቶን አካቷል። ስትራቴጂው በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ገጽ 84 ላይ እንደተመለከተው የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ማሻሻያና ማስተካከያ የሚደረግበት መሆኑን በመጥቀስ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የትምህርት ዘርፍ ልማት ለማገዝ ሲባልም የአካባቢዎቹን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሌሎች መመሪያዎች ፣ ማኑዋሎችና የአተገባበር ስልቶች እንደሚዘጋጁ አረጋግጧል። ስትራቴጂው የተንቀሳቃሽ አርብቶ አደሮችን ልዩ ልዩ ፍላጎቶች (እንስሳትን በማርባት ወቅቶችን የተከተለ ከቦታ ቦታ ዝውውር ለሚያደርጉ የህብረተሰብ ክፍሎች) እና ከፊል አርብቶ አደሮች (እንስሳት በማርባ እና ሌሎች የግብርና ተግባራትን በማዋሃድ መጠነኛ የሆነ ከቦታ ቦታ ዝውውር የሚያከናውኑ ቤተሰቦችን) ያገናዘበ ነው።

ይህ የስትራቴጂ ሰነድ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ ጉዳዮችን የሚዳስስ ሲሆን መግቢያን፣ ስያሜን፣ የ2000 ዓ.ም አርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ አፈፃፀምን፣ የ2012 ዓ.ም የአርብቶ አደር ትምህርትን ራዕይ ዓላማና ተልዕኮ የሚያስቃኝ ይሆናል። ሁለተኛው ክፍል የተከለሰው የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ስትራቴጂካዊ ተግባራትን ማለትም በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃና በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አማካይነት ትምህርትን ለዜጎች በፍትሃዊነት እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል ያሳያል። በክፍል ሶስት ስለ ዘርፈ-ብዙ ስትራቴጂያዊ ተግባራት ቀርቧል። በክፍል አራት ስር በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙት የልዩ ልዩ መዋቅሮችንና ተቋማት ሊኖራቸው የሚገባውን ተግባርና ኃላፊነቶች የተዘ ሆኖ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶችንና የአጋር አካላት አዎንታዊ ተሳትፎ ደግሞ በክፍል አምስት ስር በዝርዝር ቀርቧል።

### 1.3. የቃላት ፍቺ

አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፡-ተለማጭ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ዘዴ (modality) ሲሆን ከትምህርት ገበታ ውጭ ለሆኑ በተለይም በመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም መሳተፍ ላልቻሉ የአርብቶ አደር አካባቢ ልጆች የሚዘጋጅና ከማህበረሰቡ የአናኗር ዘይቤ ጋር አብሮ እንዲሄድ ተደርጎ የሚቀረጽ የትምህርት ፕሮግራም ነው።

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻች፡- በትምህርት ደረጃው ቢያንስ 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቀ፣ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ስልጠና የወሰደና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ በአመቻችነት የሚሰራ ነው።

ተለማጭ የትምህርት አቅርቦት ፡- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የአርብቶ አደሩን የእንቅስቃሴ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የትምህርት ካሌንደሩ፣ ሳምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት ፕሮግራሙ ከአርብቶ አደሩ የኑሮ ሁኔታና ዘይቤ ጋር ተስማሚ እንዲሆን የማድረግ አሰራር ነው።

የብዛሃ ክፍል ማስተማር ስነ- ዘዴ፡- በአንድ ክፍል ውስጥ በተመሳሳይ ክፍለ ጊዜ ሁለትና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች በአንድ መምህር/አመቻች ትምህርት የሚሰጥበት ዘዴ ነው።

አሃዳዊ የማስተማር *ስነ-ዘዴ፡-በአንድ ክፍል ውስጥ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች በሙሉ በአንድ መምህር/አመቻች የሚያስተምርበት የክፍል አደረጃጀት ነው::*

አርብቶ አደርነት፡- በእንስሳት እርባታ ላይ የተመሰረተ የአኗኗር ዘይቤ የሚከተል ማህበረሰብ ማለት ነው።

## 1.4. የአርብቶ አደር ትምህርት ነባራዊ ሁኔታዎች /Situation Analysis/

የሁኔታ ትንተናው በ2000 ዓ.ም የተዘጋጀውን የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራን መሰረት በማድርግ በአራት ዋና ዋና የአገሪቱ አርብቶ አደር አካባቢዎች ማለትም በአፋር፣ ሱማሌ፣ በደቡብ ኦሞና በቦረና ዞኖች የተከናወነ ነበር። የትንተና ውጤቱ እንደሚያሳየውም የትምህርት ተደራሽነት የተሻሻለ ቢሆንም ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ የአርብቶ አደር ልጆች የትምህርት ፍላጎት ግን በበቂ ሁኔታ አለመሟላቱን፣ እንዲሁም በስትራቴጂው ከተጠቀሱት የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ውስጥ የተተገበሩት ከፊሎቹ ብቻ መሆናቸውን ያሳያል። በአጠቃላይ በአራቱም የአርብቶ አደር አካባቢዎች የጥናት ውጤቱ በግልጽ እንደሚያሳየው፡-

- በመደበኛ ት/ቤቶችና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የዋለው ሥርዓተ-ትምህርት ከአርብቶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ ፣ ባህላዊ እድገት፣ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታና ከማህበረሰቡ የልማት ፍላጎት አንፃር ውስንነት ያለበት መሆኑ፣
- የመምህራንና አመቻቾች ቅጥርና ስልጠና ወጥነት የጎደለው ፣ ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነና ከአርብቶ አደሩ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያልተገናዘበ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ትምህርቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ አለመሰጠቱ፣
- በሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረትና ብቃት ማነስ ምክንያት ፖሊሲውንና ስትራቴጂዎቹን በተገቢው ለመተግበር የአቅም ውስንነት መታየቱ፣
- ከፍተኛ የሆነ የሠራተኞች ዝውውርና ፍልሰት በመኖሩ የተቋሙን አፈጻጸም በተከታታይነት መዝግቦ ለማቆየትና የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ ለማደረግ አለመቻሉ፣
- የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱ ደካማና ወጥነት የጎደለው በመሆኑ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ ዝግጅት እና ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ፣
- ትክክለኛና ወቅታዊ ሪፖርት የማዘጋጀት፣ መረጃን በአግባቡ በማደራጀት በጥናትና ምርምር ችግሮችን የመፍታት ስራ ውስን መሆኑ፣
- የትምህርት አጋርነት ተሳትፎ እያደገ ቢሆንም ስትራቴጂውንና ፕሮግራምን በጋራ የመንደፍና በትብብር ከመፈጸም አንጻር የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ አልነበረም።

ይሁን እንጂ የአርብቶ አደር ልማትን አስፈላጊነት አጉልተው የሚያሳዩ በርካታ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች እንደአገር የቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት ውስጥ የአርብቶ አደሩ መብቶች መካተቱ ፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መቋቋሙ፣ የአርብቶ አደር አካባቢ ልማት ፖሊሲ መቀረጹ፣ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ልማት ለማፋጠን የልዩ ድጋፍ ቦርድ መቋቋሙ፣ መንግስት ለአርብቶ አደር ልማት ያሳየውን ቁርጠኝነት ያመለክታሉ። የእነዚህ ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነትና የተለያዩ ዘርፎች በጋራ መስራት የአርብቶ አደሩን ትምህርት ለማስፋፋት መልካም አጋጣሚን ይፈጥራሉ።

በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው እና በትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች በስትራቴጂዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የተደገፉ ናቸው። ለአብነትም የተቀናጀ ተግባር-ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ (2000 ዓ.ም)፣ አገር አቀፍ የስርዓተ-ጾታ ትምህርት ስትራቴጂ (2002 ዓ.ም) እና የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ( 2004 ዓ.ም) ተጠቃሽ ናቸው።

ትምህርት ሚኒስቴር የልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት ዳይሬክቶሬትን በማቋቋም ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ወቅታዊና ውጤታማ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት አመራርና ፈጻሚዎች በተለዩ ክፍተቶችና ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ አቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት የስትራቴጂዎቹን ትግበራ በቅርበት ይደግፋል።

አገሪቱ በምትከተለው ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት መሰረት የስትራቴጂው ትግበራ እንደየክልሎቹ ነባራዊ ሁኔታ የተለያየ ነው። ከሲቪል ማህበረሰቡና አርብቶ አደር አካባቢ ካሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር አጋርነትን በመመስረት የአርብቶ አደር ትምህርትን እየደገፉ ይገኛሉ። በአሁኑ ሰዓት በእነዚህ አካባቢዎች መሠረተ ልማቱ እየተስፋፋ በመሆኑ በበርካታ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚመሩ የአርብቶ አደር ልማት ፕሮግራሞች አሉ።

### 1.4.1.የፖሊሲ ማዕቀፍ

የኢትዮጵያ መንግስት በዓለም አቀፍ የትምህርት ለሁሉም አቅርቦት ስምምነትና ትምህርትን ለሁሉም ለዜጎች ለማዳረስ ባለው ቁርጠኝነት የተነሳ ለአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልጆች የትምህርት እድሎችን ለማስፋት የሚያስችሉ በርካታ አግባብነት ያላቸው የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን አዘጋጅቷል። የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ጥራት ያለው ትምህርት የመስጠት

ዓላማን መሰረት አድርጎ የተደራሽነት፣ የተገቢነትና የፍትሃዊነት ችግሮችን እንዲፈታ ተደርጎ ተዘጋጅቷል። በዚሁ መሰረት ለአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልዩ ትኩረት በመስጠትና ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲማሩ አስችሏል። በዚህ የፖሊስ ጥላ ሥር በአርብቶ አደር አካባቢዎች የአንደኛ፣ መካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋት የሚያግዙ ተከታታይ የትምህርት ልማት ፕሮግራሞችና ልዩ ልዩ ስትራቴጂዎች ተቀርፀው ተግባራዊ ሆነዋል።

የትምህርት አቅርቦትን ከማስፋፋትና የትምህርት ተሳትፎን ከማረጋገጥ አኳያ መሻሻሎች ቢታዩም የአርብቶ አደሩን አኗኗር፣ ባህልና ወግ በበቂ ሁኔታ ያገናዘበ አልነበረም። ስለሆነም አርብቶ አደሮች ካሉባቸው ተለዋዋጭና አስቸጋሪ የአኗኗር ሁኔታዎች አንፃር ፍላጎቶቻቸውን ለማካተትና ወደ ዘመናዊ ማኅበረሰብ ለማምጣት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር አሁንም ብርቱ ጥረት ይጠይቃል።

### 1.4.2.የአርብቶ አደር ትምህርት አሁን የሚገኝበት ሁኔታ

በእድገት ወደኃላ ለቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መንግስት ልዩ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው በሀገሪቱ ህገ-መንግስት አንቀፅ 89/4 ላይ በግልፅ ተደንግጓል። በተጨማሪም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው አንቀፅ 3.7.7 በጉልህ እንዳስቀመጠው በትምህርት ዝግጅት፣ በስርጭትና በትምህርት  ግብዓቶች ድጋፍ አጠቃቀም በቂ እድል ላላገኙ ሴቶች እና ህፃናት ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ አረጋግጧል። በተጨማሪም ትምህርት ሚኒስቴር ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ከሌሎች ልዩ ድጋፍ ከሚያደርጉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር የተቀናጀ ድጋፍ ማድረግ ሲሆን ይህንኑ ተግባራዊ አድርጓል።

የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሙን መሰረት በማድረግ የመጀመሪያው አገራዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ በ2000 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሲተገበር ቆይቷል። ምንም እንኳን በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው እና በትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች ትግበራ የአርብቶ አደሮች አካባቢ የትምህርት ተሳትፎ መሻሻል ቢያሳይም ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃፀር ችግሮች ታይተዋል። ይህንንም በ2008 ዓ.ም በተካሔደው የአርብቶ አደር ትምህርት የሁኔታ ትንተና ባለፉት ዓመታት የትምህርት እድል ባላገኙ የአርብቶ አደር ክልሎችና አካባቢዎች የትምህርት ተደራሽነት፣ ጥራት፣ ፍትሐዊነትና ተገቢነት ችግሮች መኖራቸውን ማስተዋል ተችሏል።

የ2010 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ የትምህርት ስታስቲካዊ መረጃ እንደሚያሳየው በአፋር ክልል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላ በፐርሰንት ወንድ 10.4 ሴት 15.8 ድምር 13፣ የአንደኛና መካከለኛደረጃ ትምህርት ንጥር ቅበላ በፐርሰንት ወንድ 22.8 ሴት 21.5 ድምር 44.3 እና ጥቅል ቅበላ በፐርሰንት ወንድ 62.6 ሴት 56.1 ድምር 59.5 እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ (9-10) ንጥር ቅበላ ምጣኔ ወንድ 5.1 ሴት 5.9 ድምር 6.7 እና ከ11ኛ-12ኛ ክፍል ወንድ 2.5 ሴት 2.8 ድምር 3 ሲሆን ጥቅል ቅበላ (9-12) ደግሞ በፐርሰንት ወንድ 12.4 ሴት 9.2 ድምር 11 መሆኑን ያሳያል።

በሶማሌ ክልል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት (5-6 ዓመት) ቅበላ በፐርሰንት ወንድ 2.9 ሴት 2.9 ድምር 2.9፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ቅበላ በፐርሰንት ወንድ 83.9 ሴት 82.2 ድምር 83.05 እና ጥቅል ቅበላ በፐርሰንት ወንድ 105.9 ሴት 84.5 ድምር 95.6 እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ቅበላ 9-10 ወንድ 6.8 ሴት 7.7 ድምር 8.5 እና (11-12) ወንድ 3.3 ሴት 4 ድምር 4.4 ሲሆን ጥቅል ቅበላ ደግሞ (9-12) በፐርሰንት ወንድ 17.3 ሴት 12.5 ድምር 15.2 ላይ ይገኛል።

የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በአፋር ክልል 657 የመንግስትና 25 የግል በድምሩ 682 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን 35 የመንግስትና 1 የግል በድምሩ 36 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

በሶማሌ ክልል 1486 የመንግስትና 82 የግል በድምሩ 1568 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን 160 የመንግስትና 10 የግል በድምሩ 170 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተስፋፍተዋል።

እንዲሁም በ2010 ዓ.ም በአፋር ክልል በ10ኛ ክፍል ከ1.86 ነጥብ በታች ያስመዘገቡ ወንድ 1696 ሴት 966 ድምር 2662፣ 3.00 ነጥብ ያስመዘገቡ ወንድ 256 ሴት 104 ድምር 360፣ 4.00 ነጥብ ያስመዘገቡ ወንድ 3 ሴት 1 ድምር 4 መሆናቸውን መረጃው ያሳያል።

በሶማሌ ክልል ከ1.86 ነጥብ በታች ያስመዘገቡ ወንድ 392 ሴት 143 ድምር 536፣ 3.00 ነጥብ ያስመዘገቡ ወንድ 1523 ሴት 760 ድምር 2285፣ 4. 00 ነጥብ ያስመዘገቡ ደግሞ ወንድ 83 ሴት 37 ድምር 120 ተማሪዎች ናቸው።

### 1.4.3.የስትራቴጂው አፈጻጸም

የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ አላማዎች፡-

- በህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ፍትሃዊ፣ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትን ማስፋፋት፣
- በአርብቶ አደር አካባቢዎችና በሌላው የሀገሪቱ ክፍሎች መካከል ያለውን ሰፊ የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት ማጥበብ ናቸው።

በ2000 ዓ.ም የተዘጋጀው የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ተደራሽነትን ለማሻሻል በርካታ የትምህርት አቅርቦት ስልቶችንና ሥርዓቶችን አካቷል። ለአብነትም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣ አዳሪ (boarding) እና ከፊል አዳሪ (Para boarding) ት/ቤቶች ፣ ሆስቴሎች፣ መደበኛ የአንደኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ይሁን እንጂ በተጨባጭ የአማራጭ የመሰረታዊ ትምህርትን በማስፋፋት የአርብቶ አደሮችን የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ቢደረግም በተጨማሪም በተወሰኑ አካባቢዎች የአዳሪ (boarding) እና ከፊል አዳሪ (Para boarding) ት/ቤቶች ተከፍተው አገልግሎት እየሰጡ ቢሆንም የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም።

በመሆኑም በስትራቴጂው ትግበራ የታየውን ዝቅተኛ አፈፃፀም፣ ከማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ እና የትምህርት አቅርቦት ፍላጎትን ከግንዛቤ በማስገባት ከትምህርት ገበታ ውጭ ለሆኑ የአርብቶ አደር ህጻናት የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የተመዘገቡ ለውጦች፣ መልካም አጋጣሚዎችንና አዳዲስ ምክረ-ሀሳቦችን በማካተት በስራ ላይ ያለውን ስትራቴጂ መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም በትግበራው የተገኙ ስኬቶቹንና የተወሰዱ እርምጃዎችን በመፈተሽና ጥልቅ ግምገማ በማድረግ በአገሪቱ የአርብቶ አደር ትምህርት ምን እንደሚመስል የሚያሣይ የሁኔታ ትንተና ጥናት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ተከናውኗል። በዚሁ የጥናት ውጤት ላይ በመመስረት የ2000 ዓ.ም የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ተከልሶ በ2009 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም ስትራቴጂው በስራ ላይ ሳይውል የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የለውጥ ሃሳቦችን ማካተት  አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ምክረ-ሀሳቦች ተካተው ስትራቴጂው በድጋሚ በ2012 ዓ.ም እንዲከለስ ተደርጓል።

### 1.4.4.የአርብቶ አደር ትምህርት ትንተና ጥናት

በ2008 ዓ.ም በተካሔደው የአርብቶ አደር ትምህርት የሁኔታ ትንተና ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች ተለይተዋል። በዚህም መሰረት፡-

**ውጫዊ፡-** የተማሪዎች መማሪያ ቦታ ከመኖሪያ ቤታቸው መራቅ፣ ወላጆች ስለትምህርት ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ ፈቃደኛ አለመሆን፣ በገጠር አካባቢ የትምህርት ቤቶች ተደራሽ አለመሆን፣ የውሀ እጥረት፣ ሴት ልጆቻች ሊደፈሩ ይችላሉ ብለው በመስጋት ወደ ትምህርት ቤት ያለመላክ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መኖራቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

**ውስጣዊ፡-** የትምህርት ጥራት መጓደል፣ ከጥቅማጥቅም ጋር ተያይዞ የመምህራን ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት ማጣት፣ የመምህራን፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የዴስክና ሌሎች የትምህርት ግብዓቶች አለመሟላታቸው፣ የመምህራን አሰለጣጠን ስርዓት ከአርብቶ አደር የአኗኗር ዘይቤ ጋር የተጣጣመ አለመሆን፣ አርብቶ አደር ያልሆኑ መምህራን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ማስተማር አለመፈለግ ዋና ዋና ውስጣዊ ችግሮች መሆናቸውን በማረጋገጥ የቀጣይ አቅጣጭ ተቀምጧል።

### 1.4. አርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ አስፈላጊነት

ትምህርት መሰረታዊ የዜጎች መብት ከመሆኑም በላይ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ማድረስ አገራዊና ዓለም-አቀፋዊ ተቀዳሚ ተግባር ነው። የ2008 ዓ.ም የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ የክለሳ ጥናት (Survey Assessment and Revisiting) ሪፖርት እንደሚያመለክተው ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለዜጎች በማዳረስ ረገድ በመደበኛና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የላቀ ውጤት ተመዝግቧል። በተለይም በአማራጭ መሰረታ ዊ ትምህርት ፕሮግራም አማካይነት የትምህርት ተደራሽነትን ማሻሻል ተችሏል።

ይሁን እንጂ በመስኩ የተጠኑ ጥናቶችና የተዘጋጁ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት የአርብቶ አደር ትምህርት አፈጻጸም ከሌሎች አካባቢዎችና ከአገራዊ አማካይ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር አሁንም ውስንነት ያለበት በመሆኑ ተለማጭ፣ ወቅታዊና የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ፍላጎትና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የትምህርት አቅርቦት እንዲኖር በስራ ላይ ያለውን የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ በማሻሻል ፍትሃዊ፣ ጥራትና አግባባነት ያለው ትምህርት ለሁሉም የአርብቶ አደር ልጆች ተደራሽ ለማድረግ በማስፈለጉ ነው።

### 1.5. ራዕይ፣ ዓላማ እና መርሆዎች

**ራዕይ፡-** ብቁ ዜጋ የሚያፈራ ጥራቱ፣ አግባብነቱና ፍትሃዊነቱ የተረጋገጠ የትምህርት አቅርቦት ስርዓት በመዘርጋት በ2030 እ.ኤ.አ በኢኮኖሚና በማህበራዊ እድገት የዳበረ የተሻሻለ ዘላቂ የኑሮ መሰረት ያሉት አርብቶ አደር ተፈጥሮ ማየት ነው።

**ተልዕኮ፡-** ፍትሃዊ፣ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርት ለሁሉም የአርብቶ አደር ማህበረሰብ በማቅረብ ህይወታቸውን የሚያሻሽሉበት፣ ምርታማነታቸውን የሚያረጋግጡበት፣ በሀገሪቱ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ውስጥ በውጤታማነትና በእኩልነት የሚሳተፉበትንና ተጠቃሚነታቸውን የመያረጋግጡበት አቅም ለመፍጠር የሚያስችል የእውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ማጎልበቻ ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡

1.5.1.የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ዓላማ

i. የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ዋና ዓላማ

- በየደረጃው የሚገኙ መምህራንና የትምህርት አመራር ብቃትን በማረጋገጥ ፍትሐዊነቱ፣ ተደራሽነቱ፣ ጥራቱና አግባብነቱ የተረጋገጠ ትምህርት በማቅረብ ብቁ፣ ተወዳዳሪ፣ አምራች፣ አርብቶ አደሮች እንዲፈጠሩ በማድረግ አኗኗራቸውን በዘላቂነት ማሻሻል ነው፡፡

ii. የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ዝርዝር ዓላማዎች

- የትምህርት ጥራቱን በማስጠበቅ፣ ተደራሽነቱን በይበልጥ በማስፋፋትና ከቦታ ወደ ቦታ ለሚንቀሳቀሱ የአርብቶ አደር ልጆች የትምህርት ፍላጎቶች ተስማሚ የሆነ የትምህርት ማቅረቢያ ስነ-ዘዴ በመጠቀም የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ የትምህርት ፍላጎት ማርካት፣
- ሥርዓተ-ትምህርቱ ለአርብቶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ፣ ለአካባቢያዊ ዕውቀት፣ ለአካባቢው ማህበረሰብ የእድገትና የልማት ፍላጎት ተስማሚና አግባብነት ያለው እንዲሆን ማስቻልና በተገቢው የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲቀርብ ማድረግ፣
- የትምህርት አመራሮች፣ መምህራንና አመቻቾች በሥራ ገበታቸው ላይ ሊቆዩ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ በቅጥራቸው እና በስልጠናቸው ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት ጥራት ያለውና የአካባቢውን ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ትምህርት ለአርብቶ አደሩ ማቅረብ፣

- በመንግስት የአስተዳደር ተቋማት ጠንካራ የገንዘብና የሰው ሀብት ልማት በመፍጠር የስራ አመራርና የሙያ ብቃትን በማጎልበት የስትራቴጂውን ተፈፃሚነት ማረጋገጥ፣
- የትብብር አጋርነትን በመፍጠር፣ የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ የሀብትና የሰው ሀይልን በማቀናጀት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችና መመሪያዎችን በተገቢው ማሳካት፣
- ውጤታማ የክትትልና ግምገማ ስርዓት እንዲሁም የመረጃ ሥራ አመራር ማዕቀፍን በማደራጀት የአርብቶ አደር ልጆችን የትምህርት ተሳትፎና የመማር ውጤት እድገት ለመገምገም የሚያስችል አቅም የሚገነባና ለቀጣይ ስትራቴጂካዊ ውሳኔዎች ግብዓት የሚሆን እውቀት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- ትምህርት በሌሎች አገራዊና ክልላዊ የአርብቶ አደር የልማት ስትራቴጂዎች ውስጥ በተቀናጀ አሰራር ጉልህ ሚና እንዲጫወት ማስቻል ናቸው።

### 1.5.2.የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ መርሆዎች

- ለአርብቶ አደሩ የኑሮ ዘይቤ ተገቢውን ክብር በመስጠት አዎንታዊ የልማት አስተዋፅኦ ማበረከት፡-የአርብቶ አደሮች ኑሮ ክብርና ዋጋ ያለው የኑሮ ዘይቤ መሆኑን የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የትምህርት አቅርቦቱም ለአርብቶ አደሮች ኑሮ ችግር ፈቺነት፣ ደህንነት፣ እድገትና ልማት ተስማሚ እንዲሆንና አስፈላጊውን አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት መደረግ አለበት።

- **ተለማጭ የትምህርት አቅርቦት ዘዴዎችን በሥራ ላይ ማዋል፡**-ተለማጭ የትምህርት አቅርቦት ዘዴዎችን በሥራ ላይ በማዋል የትምህርት ሥርዓቱ ብዝሃነትን የሚያስተናግድ ለአርብቶ አደሩ ፍላጎትና ለአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ተስማሚ የሆነ ትምህርት ማቅረብ።
- **የአርብቶ አደሮችን የትምህርት ተደራሽነት ማስፋት፡-** አርብቶ አደሮች ከአኗኗር ዘይቤዎቻቸው ጋር በተያያዘ የመማር ዕድላቸውን ሲያመክኑ የነበሩ ተግዳሮቶችን ለመቀነስ በተለማጭ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች በመታገዝ የመማር ዕድላቸውን የማስፋት፣ የማስቀጠልና የማዳበር ስራ መስራት፣

- **ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት መቅረፅ፡-** እያንዳንዱ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት አስፈላጊውን ጥራት ያሟላ ሆኖ በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማስተናገድ በሚያስችል መልኩ የሚቀረፅ ይሆናል፡፡
- **የባለቤትነትና ቁርጠኝነት ስሜት መፍጠር፡-** ስትራቴጂው በተገቢውና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለመተግበር የትምህርት ባለድርሻ አካላት የባለቤትነትንና ቁርጠኝነትን ስሜት በመፍጠር ባለው ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት ጋር በማስማማት፣ ከአርብቶ አደር አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሆነ የትምህርት አቅርቦት ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- **ለአርብቶ አደሩ የኑሮ አማራጮችን ማስፋፋት፡-** ለአርብቶ አደሩ የሚሰጠው ትምህርት ተጨማሪ የኑሮ አማራጮችን ሊያሳይና ሊያዳብር የሚያስችል የተሟላ እውቀትና ክህሎት የሚያስጨብጥ እንዲሆን ማድረግ፡፡

# ክፍል ሁለት፡

# ስትራተጂዊ ተግባራት

## 2.1. የአርብቶ አደር ትምህርት የአቅርቦት ስልቶች

በዚህ ክፍል ልዩ ልዩ የትምህርት እርከኖች፣ መዋቅሮችና የትምህርት አቅርቦት ስልቶች፣ ተስማሚ ከሆኑ ሰትራቴጂያዊ ዓላማዎች ጋር በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1.የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ስልቶች

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን በፍትሃዊነት ተደራሽ በማድረግ የህጻናትን የትምህርት ዝግጁነትና ውጤታማነት ማሻሻል*

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናቱ የወደፊት የትምህርት ስኬት የሚገነባበት፣ አስተማማኝና ወሳኝ መሠረት የሚጣልበት መሆኑ በሰፊው ይታመናል፡፡ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትበመንግስት ትኩረት የተሰጠው ቁልፍ ሀገራዊ የፖሊሲ አቅጣጫ ቢሆንም በክልሎች መካከል ጉልህ የአፈጻጸም ልዩነት ከመታየቱም በላይ አገልግሎቱም በአብዛኛው በከተማዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ አካባቢ አገልግሎቱ አዲስ በመሆኑና አተገባበሩም ገና በጅምር ላይ የሚገኝ በመሆኑ ውስንነቶች ይታዩበታል፡፡

በእነዚህ አካባቢዎች መሠረታዊ ትምህርት የሚሰጥባቸው ተቋማት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችና አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ቢኖሩም  የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በመደበኛነት እየተተገበረ አይደለም።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለትምህርት ተሳትፎና ውጤት መሻሻል ጉልህ ሚና ስለሚጫወት ተገቢውን ሃብት በመመደብ የትምህርት ሥርዓቱን ተድራሽ ማድረግ ያስፈልጋል። በአርብቶ አደር አካባቢዎች ጥራት ያለው ትምህርትን ለሁሉም ለማድረስ ይቻል ዘንድ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲስፋፋ ይመከራል። ጥራት ያለው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በአርብቶ አደር አካባቢ ተደራሽ ለማድረግ የሚከተሉት ሶስት የትምህርት የአቅርቦት ስልቶች ቀርበዋል።

**ሀ. የኦ ክፍል ትምህርት:-** በዚህ የአቅርቦት ስልት ትምህርት ከ1ኛ ክፍል በፊት የሚሰጥና እንደ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ለአንድ ወይም ለሁለት አመታት ህጻናትን የሚያዘጋጅ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ስልት ነው። ይህ የአቅርቦት ስልት ለሁለት ዓመታት በሚሰጥበት ሁኔታ የህጻናት ዕድሜ /ከ 5-6/ የሚሆን ሲሆን በአንድ አመት ፕሮግራም ተጠቃሚ የሚሆኑት ግን ስድስት አመት የሞላቸው ይሆናሉ።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ  ፕሮግራም ኣላማ  ኦ ክፍልን በአርብቶ አደር አካባቢዎች በማስተዋወቅ እያንዳንዱ ተማሪ በቀጣይ ዕድሜው የመማር ሙሉ አቅሙን እንዲጠቀም ማስቻል   ነው። በአገራዊ ስታንዳርድ መሰረት በእያንዳንዱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችና በተንቀሳቃሽ እንዲሁም በከፊል ተንቀሳቃሽ የትምህርት ጣቢያዎች ውስጥ የሚተገበር ይሆናል።

የመርሃ ግብሩ አተገባበር ተለማጭ ሲሆን በየደረጃው ያሉ አካላት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን የማሟለት ሃላፊነት አለባቸው።  አመቻቾች ከአካባቢው ማህበረሰብ የሚመረጡ ሲሆን የአካባቢውን ቋንቋ የሚናገሩ፣ የአርብቶ አደርን ባህል የሚያውቁና የሚያከብሩ፣ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህርነት በዲፕሎማ (12+3) የተመረቁ፣ ካልተቻለ ሁለተኛ ደረጃ አጠናቀው የቅድመ ስራ ላይ ስልጠና የወሰዱ መሆን ያለባቸው ሲሆን አፈጻጸሙም ክልል ትምህርት ቢሮዎች በአቅራቢያ ከሚገኙ የመምህራን ትምህር ኮሌጆች ጋር በመመካከር የሚተገብሩት ይሆናል።

ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚያስፈልጉ የትምህርት ቁሳቁሶች (የሳይንስ ኪቶች፣ የማስተማሪያ መፅሃፍትና የተማሪዎች መለማመጃ ወረቀቶች ወዘተ) በየትምህርት ተቋማቱ ይሰራጫሉ። የክላስተር ማዕከላት አስተባባሪዎችም የመርሃ ግብሩ አተገባበርን በተመለከተ ክትትልና ግምገማ ያከናውናሉ። ህጻናትን በጨዋታ መልክ ማስተማር ይቻል ዘንድ ለህጻናቱ እድሜ የሚመጥኑ አግባብነት ያላቸው የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በስራ ላይ የሚውሉ ሲሆን የልጆቹ የትምህርት አቀባበል ዕድገታቸው በተከታታይ ምዘና የማስተማር ስነዘዴ የሚለካ ይሆናል።በተጨማሪም የዚህ የትምህርት አቅርቦት ስልት ትግበራ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ የሚተገበር ይሆናል።

**ለ.የተፋጠነ የህፃናት ትምህርት ዝግጁነት** (ASRP)፡- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዕድል ላላገኙ የ 6 ወይም 7 አመት ህጻናት አንደኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት በአጭር ጊዜ ውስጥ የቅድመ አንደኛ ክፍል ትምህርትን የሚያገኙበት መርሀግብር ነው። ፕሮግራሙ ምንም ዓይነት ተጨማሪ መሰረተ ልማትም ሆነ የሰው ሃይል የማይጠይቅና በወጪ ቆጣቢ አማራጭ በመሆኑ የአርብቶ አደር ልጆችን የትምህርት ፍላጎት ያነቃቃል። መሰረታዊ የንባብና የስሌት ችሎታን ያካተተ የተለየ ሥርዓተ-ትምህርት በማዘጋጀት በ150 ሰዓትና በ40 ቀናት እንዲጠናቀቅ ይደረጋል። ትምህርቱም የሚሰጠው በአካባቢው በሚገኙ ት/ቤቶችና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ስራ ላይ ያሉትን ግብዓቶችና መምህራንን በመጠቀም ነው። መርሀ-ግብሩ መደበኛው የትምህርት ካሌንደር ከመጀመሩ በፊት የሚሰጥ ነው።

**መ. የህፃን- ለህፃን ፕሮግራም**፡- የህፃን-ለህፃን ፕሮግራም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽ ባልሆነባቸው አካባቢዎች ለአርብቶ አደር ልጆች አማራጭና ተመራጭ ሆኖ የሚቀርብ የትምህርት አቅርቦት ስልት ነው። ፕሮግራሙ የአርብቶ አደር ልጆችን የግንዛቤ፣ የስነ ልሳን፣ የስሜትና የማህበራዊ እድገታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዳና በተገቢው የዕድሜ ክልል ውስጥ ተመጥኖ በቀረበላቸው የትምህርት ተግባራት ላይ ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚረዳ ነው። አቀራረቡ አሳታፊና ተከታታይ የትምህርት ጨዋታዎችና ተግባራትን ያካተተና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ንባብና ስሌት መሰረት የሚጣልበት ነው።

የህፃን-ለህፃን ፕሮግራም የአንድ ዓመት ፕሮግራም ሲሆን በመደበኛ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከአምስተኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል) እንዲሁም በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ውስጥ (ከደረጃ አምስት እስከ ስድስት) በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው በመምህራኖቻቸው ስልጠናና ድጋፍ እየተደረጋላቸው በአመቻችነት የሚሰሩበት

ስልት ነው። በትምህርት ዘመኑ በሳምንት ለሶስት ቀናት የሚያስተምሩ ሲሆን በዚህም አንድ አመቻች ሁለት ህፃናትን ይደግፋል። ወላጆችም ህፃናቱን የመከታተልና የማስተማር ሚናቸውን በመወጣት ትርጉም ያለው ተሳትፎ ያደርጋሉ።

አመቻቾች ንባብና ስሌትን የሚያስተምሩባቸው የትምህርት ቁሳቁሶች የያዙ ኪቶች ይሰጣቸዋል። የህፃናት የመማሪያ ፓኬጅ፣ የመምህራንና የአመቻቾች መመሪያና የስልጠና ማኑዋል የመሳሰሉት ቁሳቁሶች ተዘጋጅተው ለመምህራንና ተማሪዎች ይሰራጫሉ፡ ፡ የትምህርት ሂደቱም ስዕሎችን፣ ጨዋታዎችን፣ በዓይነት መለየትን፣ተረቶችን፣ የማዳመጥ ልምምዶችን፣ ግጥምና መዝሙሮችን ያካተተ ሲሆን ህፃናቱ የአካባቢያቸውን ቁሳቁሶች በመጠቀም በዕለት ተዕለት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፍታት የሚያስችላቸው ማጠቃለያ ላይ ይደርሱ ዘንድ ዕድል ይሰጧቸዋል። ለእድሜያቸው ተስማሚ የሆኑ የመማሪያ ቁሳቁሶችና የአተገባበር ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት የማስተማሪያ ስልቶቹ ተለማጭ እንዲሆኑ ይደረጋል። ከአርብቶ አደር አካባቢ ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሆኑ ህፃናት ከተለዩ በኋላ ወላጆች ልጆቻቸውን በፕሮግራሙ እንዲያሳትፉ የንቅናቄ ስራ ይሰራል። መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመርሀግብሩ አተገባበር ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ። በክላስተር ማዕከላት ሱፐርቫይዘሮች አማካይነት የፋይዳ ጥናት፣ የድጋፍ፣ የክትትልና የግምገማ ተግባራት ይከናወናል።

## 2.1.2.የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የአፈጻጸም ስልት

ባለድርሻ አካላት በከተማና በአርብቶ አደር የሰፈራ ጣቢያዎች አካባቢ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት (ECCE) ማዕከላትን እንዲከፍቱ ይበረታታሉ።ይህንኑ በተመለከተ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ውይይት ፎረሞች፣ የአህዝቦት ስራዎች፣ ልምድ ልውውጦች፣ የግንኙነት መረቦች አርብቶ አደሩ አካባቢ በማዘጋጀት ስለህፃናት እንክብካቤና ትምህርት አስፈላጊነት ማሳወቅ ያስፈልጋል። የንቅናቄ ስራውም የህፃናት እክብካቤና ትምህርትን በአርብቶ አደር አካባቢዎች በማስፋፋት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህጻናት ትኩረት ይሰጣል።

ለህፃናት እንክብካቤና ትምህርት/የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊው ግብዓት ተሟልቶ ከክልል ትምህርት ቢሮ እስከ ቀበሌ ድረስ የዘለቀ ተገቢነት ያለው ተቋማዊ መዋቅር ይዘረጋል። መዋቅሩም በአርብቶ አደር አካባቢ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት ፕሮግራም መተግበር የሚያስችል ልዩ ልዩ የተግባርና የኃላፊነት ክፍፍል መኖሩን የሚያረጋግጥ ነው። ስለህፃናት እንክብካቤና ትምህርት የሚደረግን የውይይት ፎረም የሚያስተባብር የህፃናት

እንክብካቤና ትምህርት(ECCE) ምክር ቤት በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ ይቋቋማል። ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌና በማህበረሰብ ደረጃ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል።

### 2.1.3. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የአቅርቦት ስልት

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *የአርብቶ አደር ልጆችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሻሻል የተለያዩ የትምህርት አቅርቦት ስልቶች (አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣ ተንቀሳቃሽ ትምህርት፣ መደበኛ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት) ተግባራዊ ማድረግና ማጠናከር፣*

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የአርብቶ አደር ህጻናት መሰረታዊውን ዕውቀት፣ ክህሎትና እሴት እንዲላበሱ በማድረግና አቅማቸውን በማሳደግ ችግር ፈቺና ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ዜጎች ለመፍጠር ያስችላል። በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ጥራት ያለው ትምህርት በአርብቶ አደር ማህበረሰብ አካባቢ ተደራሽ አለመሆን የእለት ተዕለት ኑሮአቸውንና ደህንነታቸውን በእጅጉ ይጎዳል። ህጻናቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽ ባለመሆናቸውም ለአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ መስተጋብርና እድገት የሚያበረክቱት ሚና ይቀጭጫል። ስለሆነም የሚከተሉት ስትራቴጂካዊ አማራጮችን ስራ ላይ በማዋል ጥራት ያለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአርብቶ አደር አካባቢ ለሚገኙ ህጻናት ይሰጣል።

#### i. *መደበኛ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት*

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *የነባር ትምህርት ቤቶችን ስርዓት በማጠናከርና ግብዓትና ፋሲሊቲዎችን በማሟላት የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጥ።*

ባለፉት ሁለት አስርት አመታት መንግስት የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአርብቶ አደር አካባቢዎች እንዲስፋፉ ከፍተኛ ጥረት በማድረጉ የትምህርት ተደራሽነት ተሻሽሏል። ሆኖም ግን አሁንም የተሳትፎ መጠኑ ከሀገራዊ አማካኝ ተሳትፎ በታች ነው። መደበኛው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት የከፊል አርብቶ አደር ቤተሰብ ህጻናት ፍላጎትን ሊያሟላ ቢችልም ለተንቀሳቃሽ አርብቶ አደር ልጆች ግን በተሟላ ደረጃ ተደራሽ ሊሆን አልቻለም።ይህንን ችግር ለመፍታት የአርብቶ አደሩን እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ

የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መረብ በመዘርጋት ጥራት ያለው የትምህርት አቅርቦት ቀጣይነትን ለማሻሻል የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ ተግባራት ይከናወናሉ።

- በተማሪዎች መኖሪያ ቤትና በትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ርቀት ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ማስፋፋት፣
- የአርብቶ አደሮችን የእንቅስቃሴ መስመሮች (ርቀቱን፣ ጊዜውን፣ የእንቅስቃሴ መጠን፣ ምቹና ምቹ ባልሆነ የአየር ንብረት ጊዜ ያላቸው የእንቅስቃሴ ሆኔታ) በማጥናት ለትምህርት ቤቶች ግንባታ ስርጭት (ካርታ ስራ) የሚረዳ መረጃ መሰበሰብ።
- የህዝብ ብዛት በበቂ ቁጥር ባሉባቸው አካባቢዎች መደበኛ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ ቤቶችን መገንባት፣
- በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች አቅራቢያ የውሃ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ፤
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን ወደ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማሳደግ የከፊል አርብቶ አደር ህጻናትን ተደራሽ ማድረግ።
- ለአካባቢው ተስማሚና ተለማጭ የሆነ የትምህርት ዘመን ካላንደር በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፤
- ምቹና ተለማጭ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ ስነ-ዘዴ መተግበር፤
- የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤
- የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ጥራትና ምቹ ሁኔታ በማሻሻል፣ ህጻናትን በትምህርት ገበታቸው ላይ ማቆየትና የትምህርት ውጤታቸውን ማሳደግ፤
- በሁሉም ት/ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶች፣ የትምህርት ቁሳቁሶችና የመማሪያ መሳሪያዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ።
  - ተማሪዎች የውሃና የመፀዳጃ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
  - ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና (CPD) ተግባራዊ ማድረግ፤
  - በሁሉም የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባር ተኮር ትምህርትን ማስተዋወቅ፤
  - የተማሪዎቹ ቁጥር አነስተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች የበዛሂ- ክፍል የማስተማር ስነ-ዘዴ /Multi grade system / ተግባራዊ ማድረግ፤

- ከማዕከል ርቀው በሚገኙ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ለሚያስተምሩ መምህራን ልዩ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፤
- ርቀው ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች በልዩ ሁኔታ ተጨማሪ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- ለአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የክላስተር የአገልግሎት ማዕከላትን ማቋቋም፤
- ተማሪዎች ከአንደኛና መካከለኛ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያደርጉትን ሽግግር ለማቀላጠፍ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ቤቶችና በመጋቢ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች መካከል የክላስተር መረብ መፍጠር፤
- ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የትምህርት ቤት ምገባ፣ የትምህርት ቁሳቁስና ነፃ የትምህርት እድል መስጠትና ወዘተ--- እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

ii. አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት

**ስትራተጂያዊ ዓላማ፡-** *በስራ ላይ ያሉ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን ማጠናከር፣ ማሳደግና ስርዓት መዘርጋት እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ አዳዲስ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን ማቋቋም።*

አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የተደራጀ የመሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ሆኖ በዋናነት በባህሪው ተለማጭና በተጠቃሚው ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ እንዲሁም ከመደበኛው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ውጪ የሆነ ስርዓት ነው። ለመደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት እንደ አማራጭ ሆኖ የቀረበ ሲሆን በስድስት ዓመታት የሚጠናቀቅ መርሃ ግብር ነው። በ2008 የተዘጋጀው የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተመራጭ ስልት መሆኑን ያሳያል።

ምንም እንኳ መርሀግብሩ የትምህርት ተደራሽነት ከማረጋገጥ አኳያ አስተዋፅኦ ቢኖረውም አርብቶ አደሩ ለከብቶች ውሀና ምግብ ፍለጋ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ተማሪዎችን የማቆየት አቅሙ ውስን ነው። መርሀ ግብሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በተለያዩ ዘዴዎች ለመስጠት የተቀረፀ ሲሆን ተማሪ ተኮር፣ ተለማጭ የጊዜ ሰሌዳና የማስተማር ስልቶችን መጠቀምን ያጠቃልላል ። ከዚህም በተጨማሪ ወጪ ቆጣቢ ግንባታ መጠቀም፣ከአካባቢው ማህበረሰብ በሚመለመሉ አስተባባሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማርና ለተዘነጉ

የህብረተሰብ ክፍሎች (ተንቀሳቃሽ አርብቶ አደሮች) ትኩረት ትኩረት መስጠት ላይ ያተኩራል ፡፡

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ዋነኛው ጠቀሜታ በተለማጭ ሁኔታ ትምህርትን ማስቀጠል ቢሆንም ፕሮግራሙን ሙሉ በሙሉ ለሁሉም የአርብቶ አደር ልጆች ተደራሽ ማድረግ አልቻለም። ይህ በጥራቱ ላይና እጅግ አስፈላጊ በሆነው የትምህርት ተለማጭነት ላይ ጉዳት እያደረሰ ስለሚገኝ ጥራቱንና አስተዳደሩን ለማሻሻል የሚረዳ ልዩ የአሰራር ስርዓት መፍጠር ያስፈልጋል። ለአርብቶ አደር አካባቢ ልጆች ጥራት ያለው አማራጭ መሰረታዊ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን የሚከተሉት ስትራቴጂዎችና ተግባራት በስራ ላይ ይውላሉ።

### ሀ/ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ስርዓት ዝርጋታ

- አማራጭ መሰረታዊ ትምህርትን በወጥነት የየክልሉ የትምህርት ስርአት አካል እንዲሆን ማድረግና ትክክለኛውን መዋቅርና አስፈፃሚ አካል እንዲኖረው ማድረግ፤
- ዋና ዋና ፈፃሚዎችና ባለድርሻ አካላት ስለ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አሰጣጥ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ዓላማውን፣ ስትራቴጂውና ግብዓቶቹን ተገንዝበው የአፈፃፀም መመሪያና ስታንዳርዱን በጥብቅ ዲሲፒሊን እንዲከተሉ ማድረግ፤

### ለ/ የአመቻቾች ቅጥርና ስልጠና ስርዓት ማሻሻል

- አመቻቾችን ከአርብቶ አደር ማህበረሰብ በመቅጠር በትምህርቱ ላይ ያላቸውን እውቀት (የአርብቶ አደር ማህበራዊ ህይወት፣ አካባቢያዊ ሳይንስ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ወ.ዘ.ተ) ለማዳበርና አግባብነት ያለው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን (ተግባር ተኮር ትምህርት ፣ የብዛሂ ክፍል አመራር ስነ ዘዴ (Multi Grade Teaching Approach) ወ.ዘ.ተ ለመጠቀም እንዲችሉ ስልጠና መስጠት፣
- የየአካባቢውን ቋንቋ መናገር የሚችሉ አመቻቾችን መቅጠር እንዲሁም ልዩ ማበረታቻና ጥቅማጥቅም ማመቻቸት፤
- ሴቶች የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻቾች እንዲሆኑ ማበረታታት፣
- የአመቻቾች ስልጠናና የሰርተፊኬት አሰጣጥ ስርዓት በማዘጋጀትና ተቋማዊ በማድረግ ስልጠናው የአርብቶ አደር ማህበረሰቡን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ። ይህም የሚሆነው

- አመቻቾች ከወላጆቻቸው ጋር አብረው የሚመጡ ጨቅላ ህፃናትና በተለያየ የእድሜና የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በዛሂ ክፍልና ተግባር ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴ በመጠቀም እንዲያስተምሩ በማስቻል፤
- የነባር አመቻቾችን የትምህርት አሰጣጥ ክህሎትና እውቀት በማሳደግ፣
- የአመቻቾች የስልጠና ፕሮግራም ከሚፈለገው ብቃትና ጥራት ጋር የተስማማ እንዲሆኑ በማስተካከል፣
- የተፋጠነ የመምህራን/አመቻቾች/ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የስልጠና ስርዓት በማስተዋዋቅ፣
- ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚያድጉ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ውስጥ ለሚመደቡ አመቻቾች የሚያስፈልጋቸውን የመሸጋገሪያ ስልጠና በማዘጋጀት፣
- ክልል የትምህርት ቢሮዎች ከመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ጋር በመነጋገር የአመቻቾች የስልጠና ጊዜ ከማህበረሰቡ የትምህርት መርሀ ግብር ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ፤
- በረሃማ በሆኑ አካባቢዎች ለሚመደቡ አመቻቾች ሳቢ የማበረቻቻ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ፤

***መ/ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት የስራ አመራር ስርዓት ማሻሻልና መዘርጋት፣***

ተቆጣጣሪዎችንና የስራ ኃላፊዎችን በሚፈልገው መጠንና ጥራት በክልልና በወረዳ ደረጃ በመቅጠር በአግባቡ እንዲሰለጥኑ ማድረግ። ይህም የሚሆነው፡-

- ተጨማሪ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተቆጣጣሪዎችን በመመደብና ሞተር ብስክሌት/ተሸከርካሪ ተመድቦላቸው ተደጋጋሚ ቁጥጥርና ድጋፍ እንዲያደርጉ በማስቻል አካባቢው ለሞተር ብስክሌት የማይመች ከሆነ ለክትትል ግምገማና ለቁጥጥር ስራ የሚውል ወጪ ለወረዳው የትምህርት ፅ/ቤት ተጨማሪ የመጓጓዣ በጀት መመደብ፤
- ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ስራ አመራር ተቆጣጣሪዎችና አስተባባሪዎች አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ላይ ያተኮረ ስልጠና በመስጠት የመርሀ ግብሩን አገልግሎት እንዲያጠናክሩ በማድረግ፣
- ለአዳዲስ የስራ ኃላፊዎች የግንዛቤ መፍጠር ስራ በመስራት የሰራተኞችን ከስራ የመልቀቅ ችግር እንዲቀርፉ በማድረግ፣

- የአመቻቾችን የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በመጠቀም ማንነታቸውንና የስራ አፈፃፀማቸውን መዝግቦ በመያዝ፣ ይህም ስልጠናዎችን ለማቀድ ፣ የሙያ ማሻሻያ ፍላጎቶቻቸውን ለማወቅና ለማገዝ ይረዳቸዋል።

አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት የቁጥጥርና የሙያ ድጋፍ መረብ እንዲኖራቸው ለማስቻል በቅርብ ከሚገኙ የጉድኝት ማዕከላትና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር ትስስር መፍጠር፣ ይህን ለማድረግ የአንደኛ ደረጃ ት/ ቤቶች መጋቢ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትን የመደገፍ ሚናቸውን እንዲወጡ በማድረግ፣

### ሠ/ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት የስራ አመራር ኮሚቴን አስተዳደራዊ አቅም ማጠናከር

- ለአካባቢው ማህበረሰብ፣ ለቀበሌ አስተዳደር፣ ለማዕከላት የስራ አመራር ኮሚቴዎች አግባብነት ያላቸውን ስልጠናዎች በመስጠት የስራ አመራር ብቃትንና ቁርጠኝነት ማሻሻል፣
- የማዕከላቱን ስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ማዕከሉን የማስተዳደር ኃላፊነትና ሚና መከለስና ማጠናከር እንዲሁም ማህበረሰቡን የማሳተፍና የማንቀሳቀስ ስራዎችን መስራት፣

### ረ/ ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ውጤታማ ትግበራ የሚረዱ መሰረተ- ልማቶችን ማስፋፋት፡-

- እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትን በተመጣጣኝ ወጪ በቀበሌዎችና በወረዳዎች መገንባት እንዲሁም አርብቶ አደሮች በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች የሚገኙ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተቋማት አገልግሎት እንዳይቋረጥ ማድረግ፣
- አዲስና ነባር መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ውሃ በሚገኝባቸው ቦታዎች ብቻ እንዲቋቋሙ ማድረግ፣
- አመቺ መፀዳጃ ቤቶችን መገንባት፣ የትምህርት ቤት ምገባን ማስቀጠልና የአርብቶ አደሩን እንቅስቃሴና የአሰፋፈር ሁኔታ በጥብቅ በመከታተል የትምህርት አቅርቦትን ማሳለጥ፣
- ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት አስፈላጊውን በጀትና የትምህርት ቤት ድጋፍ በማድረግ፣ መሰረታዊ አገልግሎቶችንና ቁሳቁሶችን (በፀኃይ ሀይል የሚሰሩና

ለማታው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ የሚውሉ ሶላር አምፖሎች) ወዘተ እንዲሟሉና ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፤

1. የተማሪዎችን ብዛት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተለማጭነቱን በጠበቀ መንገድ የተመረጡ መሰረታዊ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ደረጃ ማሳደግ፣
2. ተለማጭነትን በመጠቀም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አማራጭነት ማስቀጠል ከአርብቶ አደር ማህበረሰብ ጋር በመመካከር የወቅቶችን ሁኔታ ያገናዘበ አመቺ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ምቹ የትምህርት ፕሮግራም ማካሄድ፣

- ተለማጭና ለአካባቢው አግባብነት ያለው ወቅታዊ የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ ለተለያዩ ክልሎችና ዞኖች ማዘጋጀት። የትምህርት ጊዜ ሰሌዳውም ደረቅና እርጥብ ወቅቶችን፣ የአርብቶ አደሩን የእንቅስቃሴ ሂደት፣ መዳረሻዎችን እንዲሁም የአሰፋፈር ሁኔታዎችን ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ።ከዚህም በተጨማሪ የጊዜ ሰሌዳው በትምህርት አሰጣጡ፣ በአርብቶ አደር እንቅስቃሴና የከብቶች እርባታ ስራ ጋር መጋጨት የለበትም።
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ክፍለ-ጊዜና የአመቻቾች የስራ ላይ ስልጠና የጊዜ ሰሌዳ የሚጣረሱ እንዳይሆኑ ማድረግ፣
- ከማህበረሰቡ ጋር በመመካከር የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት የትምህርት ቀን መርሃ-ግብር ተለማጭና አግባብነት ያለው እንዲሆን ማድረግ፤
- ‹‹የተማሪዎች የመረብ ካርድ መጠቀም ›› ይህ ካርድ ተማሪዎች ወደ ሌላ ማዕከል ሲዛወሩ የትምህርት ሁኔታቸውን የሚያሳይ ነው። የአያያዝ ስርዓቱን በማዛመን ከእያንዳንዱ የአገልግሎት ወቅት በኃላ ካርዱን በመገምገም እና እንዳስፈላጊነቱ ማስተካከያዎችን በማድረግ ተማሪዎች ወደ ሌላ ማእከል ወይም ወደ መደበኛ ት/ቤቶች ሲዛወሩ ችግር እንዳይገጥማቸው ማገዝ፤
- በመረብ ካርድ (Network Card) የሚመዘገቡ ጊዜያዊ ተማሪዎችን ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉበትን ስልት ለአመቻቾች ስልጠና መስጠት፣

3. የስርዓት ትምህርቱንና የመማሪያ ቁሳቁሶችን ጥራትና አግባብነት ማሻሻል።
    - የአርብቶ አደሩን የአኗኗር ሁኔታ በስርአተ ትምህርቱ ይዘት ውስጥ እንዲካተት በማድረግ የሀገር በቀል እውቀት እንዲስፋፋ፣
    - የማስተማሪያ ቋንቋው በአካባቢው የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ፣

- መንግስታዊ ፣መንግስታዊ ያልሆኑና የሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ምቹ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችሉ የትምህርት መሳሪያዎችን በአካባቢው ቋንቋ ማዘጋጀት፤
- ቤተ መፅሀፍት (በግመልና በአህያ ሊጓጓዙ የሚችሉ) በማስፋፋትና የንባብ ግብዓቶችን በማቅረብ የንባብ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ፣
- አማራጭና አግባብነት ያላቸውን ቴክኖሎጂዎች (ማታ ላይ ለመማር የሚረዱና በፀሀይ ሀይል የሚሰሩ መብራቶችን) ማስተዋወቅ እንዲሁም ዲጂታል ኤሌክትሮኒክ ትምህርቶችንና ደጋፊ የትምህርትና የንባብ መረጃዎችን ማቅረብ፣

### iii. የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *የተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት በመጠቀም የተንቀሳቃሽ አርብቶ አደር ልጆችን የመሰረታዊ ትምህርት ተደራሽነት ማስፋፋት።*

የተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መርሃ-ግብር ትምህርትን በተፈለገው ጊዜና ቦታ ለአርብቶ አደር ልጆች ማቅረብን ዓላማው ያደረገ ሲሆን ከቦታ ቦታ ለሚንቀሳቀሱ የአርብቶ አደሩ ልጆች የኑሮ ሁኔታ በተከተለ መልኩ የትምህርት ተደራሽነትን ይጨምራል። ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ተማሪዎች በአንድ ቦታ ጊዜና አካባቢ ሳይገደቡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም እንዲያገኙ ያደርጋል። ይህ አሰራር በማይቋረጥ እንቅስቃሴና አኗኗራቸው የሚጠይቃቸውን የስራ ሁኔታ በማያስተጓጉል መልኩ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያስችላል።

ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ለተንቀሳቃሽ አርብቶ አደሮች ተደራሽነትንና ትምህርትን ሳያቋርጡ መቀጠል የሚያስችል ግልፅ አቅም ያለው ሲሆን አንድ የአፋር አዛውንት እንዳሉት << እግሮች ያሉትና ከኛ ጋር መንቀሳቀስ የሚችል ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ካመጣችሁልን እንማራለን>> ብለዋል።ነገር ግን የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ተንቀሳቃሽ ማድረግ አመቻቾችን ከመቅጠር ፣ ከማስተዳደር ፣ ከመቆጣጠር ከማሰልጠንና በስራ ላይ ከማቆየት አንፃር እንዲሁም በአስቸጋሪውን ሁኔታ ውስጥ ምን ያህል በቁርጠኝነት ተማሪዎች እያስተማሩ እንዳለ ከማረጋገጥ አኳያ ተግዳሮቶቹ ብዙ ናቸው። በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚገኙ የተንቀሳቃሽ አርብቶ አደር ልጆች መሰረታዊ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ የሚከተሉት ስልቶችና ተግባራቶች ይፈፀማሉ።

1. በተለያዩ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ውስጥ ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አዋጪነትን መፈተሽ

- የተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን የሙከራ ፕሮግራም መንደፍና በአንዳንድ የተመረጡ ወረዳዎች ላይ መተግበር፣
- ስለተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጥቅም ለጎሳ መሪዎች /አባ ገዳዎች በማስረዳትና በማማከር አኗኗራቸውንና ባህላዊ እሴቶቻቸውን በአከበረ መልኩ ትምህርቱን ማቅረብ፤
- በአንድ አባወራ ስር ለሚተዳደሩ የጎሳ አባላት ወይም የቤተሰብ ስብስቦች ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መክፈት። ይህንን ዓይነት ሞዴል ለመተግበር የሚያስችለው ትንሹ የቤተሰብ ቁጥር ከጎሳ አባላት ጋር የሚመከር ሆኖ ይህ እንደ እንቅስቃሴው ወቅት ሊቀየር የሚችል ይሆናል፣
- የአርብቶ አደር ማህበረሰቡን ባህላዊ አደረጃጀቶች፣ ጎሳዎችን የገዳ ስርአቱንና ተደማጭነት ያላቸውን የህብረተሰብ ተወካዩች ስለተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አሰጣጥ ያላቸውን ግንዛቤ ማዳበርና የአመራርና የባለቤትነት ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ፤
- ድጋፍ ሰጪዎች፣ የጎሳ መሪዎችና የተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመቻቾች በታዩ መሻሻሎችና በአጋጠሙ ተግዳሮቶች ላይ ውይይት በማድረግ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣

2. ለተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች አስፈላጊ ግብአቶችን ሟሟላት

- ለጣቢያዎቹ ድጋፍ የሚሰጡ መሰረተ ልማቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፤
- አመቻቾችን በመቅጠር የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት እንዴት በተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች እንደሚተገበር ስልጠና መስጠት፣
- ለጣቢያዎቹ የሚያገለግሉ የመቀመጫ ምንጣፍ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣የመፅሐፍት ማስቀመጫ ሳጥን ወዘተ-- በማቅረብ ቁሳቁሶቹና መምህራን የሚጓጓዙበትን ትራንስፖርት ማዘጋጀት።
- ምሽት ላይ ለመማር የሚያስችሉ በፀሃይ ሀይል የሚሰሩ መብራቶችን ማቅረብ፤
- በቀላሉ ሊገጣጠሙና ሊፈቱ የሚችሉ እንዲሁም በጋማ ከብቶች ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ << የድንኳን ክፍሎች >> ማቅረብ " እነዚህም ድንኳኖቹ

ከባድ ሳይሆኑ ቀላል አልሙኒየም ምስሶዎች ያሉት ወይም ከአከባቢው በተገኙ ቁሶች በቀላሉ የሚፈርስና የሚሰሩ እንዲሁም ባህላዊ ጎጆዎችን መስሪያ ሊሆን ይችላል።

- የዛፍ ጥላ፣ በአካባቢው የሚገኙ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ወይም ባህላዊ የድንኳን ቤቶችን እንደ አማራጭ ተንቀሳቃሽ ትምህርት ጣቢያ << መማሪያ ክፍል>> መጠቀም ይቻላል።
- ለእያንዳንዱ አመቻች ድንኳን፣ አልጋ ፣ በፀሀይ ኃይል የሚሰራ መብራትና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች መስጠት፣
- እንደ ተንቀሳቃሽ ማህበረሰቡና ተማሪዎች ብዛትሁሉም ተማሪዎች መማር ይችሉ ዘንድ ሁለት አስተባባሪዎችና ከአንድ በላይ የድንኳን መማሪያ ክፍሎች/ከለላዎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች እድሜያቸውና ደረጃቸው የተለያየ ልጆች ሁለተኛ ድንኳን ሳያስፈልጋቸው በተለያዩ ጊዜያት መማር ይችላሉ።
- ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ የበጀት ድጋፍ (School grant) እና የምገባ ፕሮግራም (School feeding) ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የመማሪያ ማንዋሎች፣ሲለበሶችና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች ወደ ሚፈለጉበት ቦታ እንዲሰራጩ ማድረግ፣
- ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ቤተመፃህፍቶችን ግመል/አህያ በመጠቀም ማቋቋምና በእንቅስቃሴ መንገዳቸው ላይ ተጨማሪ ቁሶችን በመስጠት ትምህርታቸውን መደገፍ።እንደ ተንቀሳቃሽ ስልክ ያሉትን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ሞዴል ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን መደገፍ፣
- የሬዲዮ አገልግሎት የሚሰጡና ሜሞሪ ካርድ ሊወስዱ የሚችሉ በፀሃይ ኃይል የሚሰሩ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን በትንሽ ዋጋ በማቅረብ በተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ለሚመዘገቡ ተጠቃሚ አርብቶ አደሮች ማደል፣
- ተጨማሪ ትምህርቶችን በተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ በሜሞሪ ካርድና በሬዲዮ ፕሮግራሞ ለተማሪዎች ማድረስ፣
- ለአመቻቾች ተንቀሳቃሽ ስልኮችን በመስጠት አርብቶ አደሮቹ ጋር እየደወሉ የተማሪዎቻቸውን የትምህርት ሁኔታና የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመለየትና ለመፍታት እንዲችሉ ማድረግ፣
- ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ላይ ድጋፍ ለመጠየቅና ለሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ማብራሪያዎችን ለመጠየቅ ወደ አመቻቾቻቸው እንዲደውሉ ማበረታት፤

- አመቻቹ ስልክ በመደዋወል እርስ በርስ ልምድ እንዲለዋወጡ ማድረግ፣
- የኔትወርክ ካርድ ስርዓቱን በመጠቀም የተማሪዎቹን የትምህርት ጣቢያ ቅያሬና የትምህት ቀጣይነትን ማረጋገጥ፣

3. ለተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ የትምህርት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት

- የወረዳ ኃላፊዎች፣ የጎሳ መሪዎችና የመንደር/የቤተሰብ ኃላፊዎችን ባሳተፈ መልኩ ውጤታማ የትምህርት አስተዳደር የክትትልና ግምገማ ዘዴዎችን መፍጠር፣
- የአካባቢውን የመንግስት የስራ ኃላፊዎችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑና ማኅበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችን፣ የጎሳ አደረጃጀቶችንና የገዳ ስርዓቶችን በማሳተፍ ተከታታይና የማያቋርጥ የተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፤
- እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ እና በወረዳ ትምህርት ፅ/ቤቶች በአካል በመገኘት ክትትል ማድረግ፣ በስልክ መጠየቅ ወይም የተማሪ መከታተያ መንገዶች በመጠቀም ሊተገበር ይቻላል።
- የጎሳ መዋቅሩና ድርጅቱ ወይም የገዳ ስርዓቱ ግልፅ ኃላፊነትን ወስደው ተንቀሳቃሽ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን መምራትና የአመቻቾችንና የመማር ማስተማር ቁሳቁሶችን ደህንነት በመጠበቅ ረገድ ዋና የስራ ድርሻቸው እንዲሆን ማድረግ፣

### 2.1.4.ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

**ስትራቴጂያዊ አላማ፡-** *የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት፣ ጥራት እንዲሁም የተማሪዎች የትምህርት ክትትልና ውጤታማነት መጨመር።*

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ማስፋፋት ድህነትን ለመቀነስ፣ እኩልነትን ለማረጋገጥ፣ ማህበራዊ ትስስርን ለማዳበርና የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ በኢኮኖሚ ተወዳደሪ እንዲሁም ከአድልዎ የፀዳ ስርዓትን ለማስፈን መሰረት የሚጥል ነው። በአንፃራዊ ሁኔታ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአርብቶ አደሮች አካባቢ ጥሩ ሽፋን ያለው ቢሆንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን አሁንም አነስተኛ ነው።በመሆኑም የአርብቶ አደር ልጆች ትምህርታቸውን የማሻሻልና የመቀጠል ወይም ህይወታቸውን ለማሻሻል ትምህርትን

የመጠቀም እድላቸው የጠበበ ነው። ጥቅልም ሆነ ንጥር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን ከሀገራዊ አማካኝም በጣም ያነሰ ነው።

በእነዚህ አካባቢዎች አብዛኛዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጥቂት የከተማ ማዕከላት የሚገኙ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ከመጋቢ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ርቀው ስለሚገኙ የተማሪዎች ከአንደኛ ወደ መካከለኛ ከዚያም ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከዚያም ወደ ከፍተኛ ትምህርት የመሸጋገር እድላቸው እጅግ አናሳ ነው።ውሱን የት/ቤቶች ስርጭት ከዝቅተኛ መሰረተ ልማትና ውሱን ግብዓት ጋር ተዳምሮ የአርብቶ አደር ማህበረሰቡን የእኩል ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ አዳጋች አድርጎታል:: ስለሆነም በርካታ ልዩ ልዩ ስትራቴጂያዊ አሰራሮችን ተቋማዊ በማድረግ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት የተሳለጠ ጥረት ይደረጋል።

## I. መደበኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**ስትራተጂያዊ ዓላማ፡-** *በአርብቶ አደር አካባቢዎች መደበኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በማስፋፋትና በማጠናከር ተደራሽነትን፣ ጥራትን፣ የተማሪዎች የትምህርት ክትትልና ውጤታማነት መጨመር።*

በአርብቶ አደር አካባቢዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላን መጨመር ተከትሎ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎና ጥራት ለማሳደግ አጠቃላይ የትግበራና የስትራቴጂ እንቅስቃሴዎች ያስፈልጋሉ።ይህም የመማሪያ ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋት፣ ለተማሪዎችና ለመምህራን ድጋፍ መስጠትና ባለድርሻ አካላትንና አጋሮችን ማንቀሳቀስ ላይ ማተኮርን ይጠይቃል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማስፋፋት የሚከተሉት ስልቶች ስራ ላይ ይውላሉ ፡-

1. አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች ተጨማሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን መገንባትና ከአንደኛና መካካለኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚደረገውን ሽግግር በማረጋገጥ የትምህርት ተደራሽነት ማሳደግ ፣
2. መሰረተ ልማቶችን በማሟላት የ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ጥራት ማሻሻል
    - ለመምህራን የመኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
    - በትምህርት ቤቶች የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል በማቋቋም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
    - አስተማማኝ የመብራትና የውሃ አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ፣

- የመማሪያ መርጃዎች የተጫኑባቸውና በፀሃይ ኃይል የሚሰሩ ታብሌቶችና የእጅ ስልኮችን በመጠቀም የኮምፒውተር ቤተ ሙከራና በኢንተርኔት የመማር እንድሎችን በመፍጠር፣ አይሲቲን ማቅረብና እንዲሁም ሌሎች የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚደግፉ እንደ ቤተ መፃህፍትና የተደራጁ ቤተሙከራዎች እንዲዋቀሩላቸው ማድረግ፣

3. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በክላስተር በማደራጀት ግብአቶችን እንዲጋሩና መምህራን ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ማስቻል፣
4. የመምህራንን ሙያዊ ብቃት ማሻሻል፣
5. በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያሉ ተማሪዎችን የትምህርት ክትትልና የትምህርት ውጤት ለማሳደግ በርካታ የድጋፍ ዘዴዎችን ማቅረብ፤ እነዚህም ልዩ የትምህርት ድጋፍ (ቱቶሪያል) መስጠት፣ በግብዓት መደገፍ፣ ልጃገረዶችና የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች እንዲሁም የመማር ፍላጎት ኖሯቸው ለተቸገሩ ልጆች ነፃ የትምህርት እድል መፍጠር፤
6. የክትትልና ግምገማ መርሃ ግብሮችን በማሻሻል ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መደበኛ ምልከታና ድጋፍ እንዲደረግ ማገዝ፣

## II. የከፊል አዳሪ ትምህርት ቤት

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *የከፊል አዳሪ ት/ቤቶችን አደረጃጀት በአርብቶ አደር አካባቢዎች በማስፋፋትና በማጠናከር የትምህርት ተደራሽነት፣ ጥራት፣ የተማሪዎች የትምህርት ክትትልንና ስኬታማነት መጨመር።*

ይህ ስርዓት አኗኗራቸው ትምህርትን ከሚያገኙባቸው ቦታዎች በጣም አርቆ ለሚወስዳቸው የአርብቶ አደር ልጆች የማደሪያና የምግብ አገልግሎች የማቅረብ ስራ ነው። የከፊል አዳሪ ትምህርት ቤት ልጆች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ከማስቻሉም በላይ ወደፊት ከአርብቶ አደር አምራችነት ህይወት ተላቀው የኑሮ መስመራቸውን በመደበኛ ትምህርት መቀጠል ለሚፈልጉ የአርብቶ አደር ልጆች የተመቻቸ ነው። ለተማሪዎቹ የተሟላ የመደበኛ ትምህርት እስከ 12ኛ ክፍል በመስጠት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመሸጋገር የሚያደርጉትን ጥረት ይደግፋል። ከዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ የሚመጡትን ተማሪዎች የኑሮ ክፍተት የሚሞላ ሆኖ ልጆቹን ከቤተሰቦቻቸው የሚነጥልና ጥራት ያለው ትምህርት እዲያገኙ ለማድረግ ያልተቋረጠ የበጀት አቅርቦትን ይጠይቃል።

በ2000 ዓ.ም የአርብቶ አደርትምህርት ስትራተጂ ውስጥ የታቀፈው ይህ አሰራር አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የአዳሪ ት/ቤቶችን በክልልና በዞን ከተሞች በማቋቋም በውሱን ደረጃ እየተተገበረ ይገኛል። ከሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃዎች የሚመጡትን ከፍተኛ የሆነውን የአርብቶ አደር ልጆች የትምህርት ፍላጎቶችን ለሟሟላት አቅርቦቱ ሊያስተካክለው አልቻለም።ተጓዳኝ የአዳሪ ት/ቤቶች የገቡት ልጆች የቤት ውስጥ ኃላፊነት ስለሌለባቸውና በተለይም ሴቶቹ ወደ ትምህርት ቤት በሚያደርጉት ጉዞ ላይ የደህንነት ስጋት ስለቀረላቸው የትምህርት አቀባበላቸው ይሻሻላል።

ይህ ስትራቴጂ መስፋፋት ይኖርበታል፤ ይሁንና የጥራት ስታንዳርዱን መጠበቅን በተመለከተ ከማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር በቅርበት የሚሰሩና ጠንካራና ውጤታማ አመራር የሚሰጡ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በመጠቀም የተቀመጠውን የጥራት ስታንዳርድ ማረጋገጥ ይገባል። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በከፊል አዳሪ ትምህርት ቤቶች በኩል ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ የሚከተሉት ስልቶችና ተግባራት ይተገበራሉ፡-

- በዞን ደረጃ የአንድ ፆታ ከፊል አዳሪ ትምህርት ቤቶች ህንፃዎችን መገንባት
  - ግንባታው ወጪ ቆጣቢ ሆኖ ነገር ግን ጥራቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፤
  - የግንባታው ቦታ (የውሃ አቅርቦትን ጨምሮ) አመቺ መሆኑንና ት/ቤቱንም ማኅበረሰባዊ ባህልን የሚወክል ጠንካራ የትምህርት ቤት ወላጅ ተማሪ መስተጋብር ያለውና በጎሳ መሪዎችና አባላት ሙሉ ስምምነት መመረጥ አለበት፤
  - ነባሮቹም ሆኑ አዳዲሶቹ ህንፃዎች ልጆቹን ለመሳብና በትምህርታቸው ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ ጥሩ የንፅህና አገልግሎት፣ የውሃ አቅርቦት፣ አልጋ፣ አላቂ የምግብ እቃዎች፣ የመዝናኛ ማዕከላትና የቤት መፃህፍት አገልግሎት የተሟላላቸው መሆን አለባቸው።
  - ልጆቹ የተሟላ የትምህርት፣ የባህል፣ የአካል ብቃትና የማህበራዊ ህይወት ክህሎቶችን ያሳድጉ ዘንድ ተጨማሪ ድጋፍና ከቀለም ትምህርት ባሻገር ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ ማበረታታት፣
  - በትምህርት መጀመሪያ፣ በግማሽ ሴሚስተርና በዓመቱ መጨረሻ ላይ የአርብቶ አደር ተማሪዎች ከቤተሰባቸው ሲመጡና ሲመለሱ የሚያስፈልጋቸውን ትራንስፖርት ማቅረብ፣

- የከፊል አዳሪ ት/ቤቶች ስራ አመራር አባላትና ተንከባካቢዎች አዳሪ ትምህርት ቤትን የማስተዳደር ክህሎት፣ ለተማሪዎች እንክብካቤ ደህንነት" ተማሪዎችን የማማከር ክህሎቶች ላይ ጥልቅ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ ከፊል አዳሪ ት/ቤቶች ለአርብቶ አደር ልጆች ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን የሚፈጥሩ እንዲሆን ማድረግ፣
- በት/ቤቱ ባህልና በአርብቶ አደር ባህል መካከል ተቃርኖ እንዳይፈጠር በማድረግ ተማሪዎቹ የሚደሰቱበትን ህይወት እንዲመሩ ተስማሚና የሚለመድ አካባቢን መፍጠር፤
- ከአርብቶ አደር ልማት ማህበር፣ ከልማት ድርጅቶችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማ አጋርነትን በመመስረት አስፈላጊ ድጋፎችን ማሰባሰብ፣
- ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ትስስር መፍጠርና የትምህርት ጥራት ደረጃን በሚከተሉት መንገዶች ማረጋገጥ፡
  - ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ለትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ለአመራርና ተማሪዎች የስነ- ምግባር መመሪያዎችን አዘገጅቶ ማሰራጨት፤
  - የትምህርት ቤት አስተዳደር ቦርድን ከአካባቢው ማህበረሰቦች ማዋቀር፣ የስነ ምግባር መመሪያዎችና የትምህርት ስራው አፈፃፀምን እንዲከታተሉና እንዲደግፉ ማድረግ፣
- ከተቻለ የከፊል አዳሪ ት/ቤቶች የትምህርት ወጪ መጋራት ይችሉ ዘንድ የራሳቸውን ገቢ የሚያስገቡባቸውንና የኀብረተሰቡን አስተዋፅኦ የሚያሰባስቡባቸውን ስትራተጂዎች መንደፍ፣
- የከፊል አዳሪ ት/ቤቶቹ የተቋቋሙበትን ዓላማ በብቃት እንዲያሳኩና አገልግሎቶቻቸው ልጆቹን ከቤተሰቦቻቸው፣ ከባህላቸውና አኗኗራቸው ጋር እንዳያራርቃቸው የተቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ፤

## III. ሆስቴሎች

**ስትራተጂያዊ ዓላማ፡-** *ሆስቴሎችን በማስፋፋትና በማጠናከር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት፣ ጥራት፣ የተማሪዎች የትምህርት ክትትልና ውጤታማነትን ማሻሻል።*

ሆስቴሎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አካባቢ የሚመሰረቱ የተማሪዎች መጠለያዎች ናቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቅርብ ርቀት በማይገኙባቸው ቦታዎች ለተማሪዎች የመደበኛ ትምህርት ተደራሽነትን የማረጋገጥ ድጋፍ ይሰጣሉ። በአርብቶ አደር አካባቢዎች ምንም ዓይነት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎቶች በማይገኙበት ሁኔታ ሆስቴሎች ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚያደርጉትን ሽግግር ያረጋግጣሉ።

በ2000 ዓ.ም በተዘጋጀው የአርብቶ አደሮች ትምህርት ስትራቴጂ መሰረት የሆስቴል አገልግሎት በውሱን ቦታና ሁኔታ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም አቅርቦቱ ከፍላጎት ጋር አልተጣጣመም፡፡ መንግስት በገጠራማ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚያቀርባቸው ሆስቴሎች በቁጥር ጥቂት ሲሆኑ በከተማ አካባቢዎች ግን በአንጻራዊነት በተሻለ ደረጃ ይገኛሉ፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት እሰከቀጠለና በተመጣጣኝ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስካልለተስፋፉ ድረስ የሆስቴል ፍላጎቱ ከፍተኛ እንደሆነ ይቆያል፡፡ ይህ አሰራር ተፈላጊው የጥራት ስታንዳርድ ሲባል መስፋፋት እንዳለበት ይመከራል፡፡ ለዚህም ከማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር በቅርበት የሚሰሩ ጠንካራ የስራ አመራር ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

ሆስቴሎችን በመጠቀም በእነዚህ አካባቢዎች የሁተለኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ የሚከተሉት ስልቶችና ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- በስራ ላይ ያሉ ሆስቴሎችን በተገቢው መምራት፣ በግብአትና አገልግሎት ማጠናከር፣
- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽ ባልሆነባቸው ቦታዎች ከአርብቶ አደር ልማት ድርጅቶች፣ ከማህበረሰቡ አባላትና ከሌሎች ጋር ውጤታማ አጋርነትን በመመስረት የወንድና የሴት ፆታን የለዩ ሆስቴሎችን በተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ መገንባት፣
- ከጎሳ አባላትና መሪዎች ጋር በመመካከርና በመስማማት ወላጆችና ልጆቻቸው ግንኙነታቸው ሳይቋረጥ በሚኖርበት ሁኔታ ሆስቴሎችን በተመረጡና ውሃ በሚገኝባቸው ቦታዎች መስራት፣
- ለሆስቴል ሰራተኞችና ተማሪዎች ግልፅ የስነ ምግባር መመሪያዎችን አዘጋጅቶ መተግበር፣
- ለተማሪ ተንከባካቢዎች፣ ለሆስቴል ኃላፊዎችና ለማህበረሰብ አባላት የትውውቅ ስልጠና ማዘጋጀትና በጋራ በመስራት ለአርብቶ አደር ልጆች ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ፣
- በሆስቴል ውሰጥ የሚኖሩ የአርብቶ አደር ልጆች የተሟላ የትምህርት ፣ የባህል ፣ የአካል ብቃትና የማህበራዊ ህይወት ክህሎቶችን፣ የመዝናኛ ማዕከላትንና የቤተ መፅሀፍት አገልግሎት በማቅረብ እንዲያዳብሩ ማድረግ፣
- ሆስቴሎችን ለተማሪዎች ምቹና ማራኪ በማድረግ ከአርብቶ አደር ማህበረሰብ ባህልና ወግ ጋር የማይጋጭበትን ሁኔታ መፍጠር፡፡
- ሆስቴሎች የተቋቋሙበትን ዓላማ በብቃት እንዲያሳኩና ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ፣ ከባህላቸውና ከአኗኗራቸው እንዳይርቁ ለማድረግ የተቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ፣

### 2.1.5.የርቀት ትምህርት

**ስትራያጂያዊ ዓላማ፡-** *ተገቢና ተስማሚ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የርቀት ትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት።*

የርቀት ትምህርት መሰረታዊ ፋይዳው፣ ተማሪዎች በራሳቸው የትምህርት አቀባበል ፍጥነት፣ ጊዜቸውንና የመማሪ ቦታ ወስነው እንዲማሩ ማስቻሉ ነው። የርቀት ትምህርትን የሚደግፉ ቴክኖሎጂዎች በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትንና በተለይም የግብዓት ችግሮች ባሉባቸው አካባዎች የትምህርት ይዘትን ለማዳበር የሚጠቅሙ ተጨማሪ ግብአቶች ናቸው። የሬዲዩ ፕሮግራሞችን በመጠቀም የርቀት ትምህርትን ለልጆችና ጎልማሶች መደበኛውን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለማገዝ ስራ ላይ ዋለ ሀገራዊ ልምድ ያለ ቢሆንም ለአርብቶ አደሩ የተለየ ትኩረት የሰጠ አልነበረም።

በርካታ አርብቶ አደሮች ተንቀሳቃሽ ሬዲዮ በተለምዶ ለኢ-መደበኛ ትምህርት መከታተያ፣ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማግኘትና እንደ መዝናኛ መሳሪያ ሲጠቀሙበት ይታያል። የእጅ ስልኮችም እንደ ትምህርት መሳሪያ የማገልገል ከፍተኛ አቅም አላቸው። በአሁኑ ወቅት የእጅ ስልኮች መረጃን ተደራሽ በማድረግ፣ የመማር እድሎችን በማመቻቸት፣ የፋይናንስ አገልግሎትን በመስጠትና የግብይት ገቢና ወጪን እንዲሁም የግብርና እንቅስቃሴዎችን ለማቀላጠፍ ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። ስለሆነም አግባብነት ያላቸውን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የርቀት ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ ይቻላል። የርቀት ትምህርትን በአርብቶ አደር አካባቢ ባለው የትምህርት ስርአት ውስጥ ለማካተት የሚከተሉትን ስትራቴጂዎችና ተግባራት ይከናወናሉ።

- የፀሀይ ሀይልን የሚጠቀሙ መሰረተልማቶች ማለትም ሬዲዮን ተንቀሳቃሽ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችና መገልግያዎች እና መሰረተ ልማቶች እንዲገኙ ማድረግ፣
- ከ 5ኛ ክፍል እስከ ሁለተኛ ደረጃ ላሉ ክፍሎች የርቀት ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት አግባብነት ያለው ስርአተ ትምህርት ፓኬጅን በሰለጠኑ ባለሙያዎች እንዲተገበር በማድረግ የርቀት ትምህርት መስጫ መንገዶችን መተግበር
- አስፈላጊ ግብዓቶችን ለራዲዮ ፕሮግራም በማሟላት ለአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ መደበኛ ትምህርትን ማቅረብ ይቻልል። ነገር ግን የራዲዮ ስርጭት ተለማጭ ስላልሆነ ፕሮግራሙን ሊደግፉና ምሉዕነቱን የሚያረጋግጡ የጽሁፍና የገጽ ለገጽ ግኑኝነቶችን ያስፈልጋል።

- የእጅ ስልኮች፣ የሚሞሪ ካርድ ና የኤሌክትሮኒክስ ሲዲዎችን በመጠቀም መደበኛ ትምህርትን ለአርብቶ አደሩ ማቅረብ ይቻላል፤ ነገር ግን ይህ በቂ ስላልሆነ የተለያዩ የርቀት ትምህርት ዘዴዎችን ያዋሃደ የመማር ዘዴ ሊተገበር ይገባል።
- የእጅ ስልኮችንና ሲዲዎችን በመጠቀም የአመቻቾችን የማስተማር ክህሎቶች ማዳበር፣ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን ማሳለጥ፣ የመምህራን ስልጠና እና የማህበረሰብ አቀፍ የትምህርት መርሃ ግብሮች ማከናወን፤
- የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎችንና ዘመናዊ የግንኙነት ዘዴዎችን በመጠቀም የማህበረሰብ መረጃዎችን ለአ. - መደበኛ የጎልማሶች ትምህርት ማዋል፣
- ሬድዮን ከሌሎች የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎች ጋር በተጓዳኝ በመጠቀም ለትምህርት መገናኛ ዘዴነት እና የግንዛቤ ማሳደጊያ ስራዎች ማዋል፤
- የእጅ ስልኮችን በመጠቀም ስለ ትምህርት አስፈላጊነት የህዝቡን ግንዛቤ ማሳደግና ድጋፍ ማሰባሰብ፤
- የመምህራን ትምህርትና የአመቻቾች ስልጠና በርቀት ትምህርት፣ በሬድዮና በእጅ ስልክ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክ ግብዓቶች እንዲደገፍ ማድረግ፤
- በርቀት ትምህርት የመምህራንን ስልጠና ለማካሄድ የሚረዱ ቁሳቁሶችንና ዘዴዎችን ማዘጋጀት፤
- በርቀት ትምህርት ውስጥ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማሻሻል ተገቢ የመመዘኛ ዘደዎችን በማዘጋጀት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- አይሲቲን በመጠቀም የርቀት ትምህርትን መንደፍና መተግበር እንዲሁም የአሰልጣኝ መምህራንን ሙያዊ ክህሎት ማበልጸግ፣
- ቴክኖሎጂዎችንና የርቀት ትምህርትን ለመደገፍ፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ተስማሚ የምዘና ዘዴ ማዘጋጀት፣
- የርቀት ትምህርትን ለመገምገም የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ስትራቴጂዎችን በመቅረፅ የትምህርቱን ውጤታማነት መመዘን።

### 2.1.6.የተቀናጀ ተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፦** *ጥራት ያለውን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ለአርብቶ አደር ጎልማሶች ተደራሽ ማድረግ፡*

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በመሰረታዊነት የጎልማሶችን መማር ለማገዝ አስፈላጊ ነው። ፕሮግራመምን የሚከታተሉ ወላጆች የትምህርትን ጥቅም ተገንዝበው የልጆቻቸውን የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራሞች ከማበረታታት በላይ በትምህርታቸው ጥራት ላይ ክትትል እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አርብቶ አደሮች በልዩ ልዩ የልማት ፓኬጆች የተገኙ እውቀትና ክህሎቶችን እንዲጠቀሙ፣ የፅሁፍ መረጃን እንዲያገኙ፣ አዳዲስ ክህሎቶችን እንዲፈልጉና ያገኟቸውን መረጃዎችና ክህሎቶች አኗኗራቸውንና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ እንዲጠቀሙባቸው ይረዳል።

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም በከተሞች አካባቢ ተግባራዊ ለማድረግ ጅምር ሙከራዎች ቢኖሩም በገጠርና አርብቶ አደር አካባቢዎች ግን ውጤታማ አልሆነም። ምንም እንኳን በአርብቶ አደር ጎልማሶች ዘንድ መጠነኛ ፍላጎት ቢኖርም አገልግሎቱን በርቀት ተደራሽ ለማድረግ የትምህርት ክትትላቸው ቀጣይ ለማድረግ ፣ የአገልግሎ አቅርቦቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥና የመርሀግብሩን አግባብነት በማስጨበጥ ረገድ ችግሮች አጋጥመዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች አርብቶ አደሩ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻቾች ወይም ፍቃደኛ በሆኑ መምህራን አማካነት ማታ ማታ ለመማር ፍላጎት በማሳየት የራሱን የጎልማሳ ትምህርት ፕሮግራም መስርቷል። ስለሆነም አግባብነት ያለው የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በአርብቶ አደር ክልሎች እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ ይደረጋል።

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በአርብቶ አደር አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች እና ተግባራት ይከናወናሉ።

- ባለድርሻ አካላት ማለትም የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ፣ የልማት አጋሮች፣ የ የሴክተር መ/ቤቶችን (ጤና ፣ ግብርና፣ ሴቶችና ህፃናት፣ የትምህርት ፅ/ቤት ወዘተ) እንዲሁም የግብርናና የጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የብዙሃን ማህበራት ተወካዩችን በማስተባበር የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በአርብቶ አደር አካባቢዎች ማስፋፋት፣
- አግባብነት ያለው ስርአተ ትምህርትና የማስተማሪያ ቁሳቁስ ማለትም የአርብቶ አደሩን የአኗኗር ዘይቤ፣ ማህበራዊ መዋቅር፣አገር በቀል ክህሎትና እውቀትን ባገናዘበ መልኩ ማዘጋጀት፣
  - የአርብቶ አደር ጎልማሶች የትምህርት ፕሮግራም ክህሎትን ላይ መሰረት ያደረገ፣ ፣ የአኗኗር ዘይቤውን ያገናዘበና አሳታፊ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት። እንዲሁም ስርአተ

ትምህርቱ የተለያዩ ርእሶችን ማትም  የእንሰሳትእና የሰው ጤና፣ እደ ጥበብ፣ የሰላም ግንባታ፣ ግጭት አፈታት፣ የግልና የአካባቢ ንፅህና፣ የማዋለድ አገልግሎት፣ የማስላትና የንባብ ክህሎት የመሳሰሉ ይዘቶችን የሚሸፍን ይሆናል።

- ♦ አርብቶ አደር ተኮር የድህረ - ንባብ ስትራቴጂዎችንና አግባብነት ያለው ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍን ማዘጋጀት፤
- ♦ የተማረ ህብረተሰብ ሊፈጥሩ የሚችሉ የትምህርት መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ ለምሳሌ በጋማ ከብት (ግመልና አህያ) ከቦታ ቦታ የሚያንቀሳቅን፣ ቤተመፅሀፍትን በማቅረብ ሊሆን ይችላል።

❖ ውስኑን ሀብትን በአግባቡ ለመገልገል ይቻል ዘንድ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትን፣ የመደበኛ ት/ቤቶችን፣ የዛፍ ጥላዎችን፣ ተንቀሳቃሽ የድንኳን ት/ቤቶችና የመሳሰሉትን ለጎልማሶች ትምህርት ታቢያነት  መጠቀም፤

❖ የአርብቶ አደሩን ባህልና ቋንቋ የሚያውቁ አመቻቾችን መቅጠር፣

❖ በአርብቶ አደር የአኗኗር ዘይቤ ላይ እውቀት ያላቸውን አመቻቾችና ሱፐርቫይዘሮችን በተለየ መልኩ ማሰልጠንና የስልጠና ስርዓቱን ተቋማዊ ማድረግ፣

- ♦ በአርብቶ አደሮች አካባቢ የሚገኙ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆችና ዩንቨርሲቲዎች የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች የትምህርት ይዘቶችን ያካተቱ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን ቀርፀው እንዲተገብሩ አቅማቸውን መገንባት፣
- ♦ ሳቢና ማራኪ የአመቻቾች የክፍያ ስርአት፣ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች የትምህርት ስታንዳርድ፣ መመሪያዎችና መፅሃፍትን በየደረጃዎቹ ማዘጋጀት፣
- ♦ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ለመተግበርና ለአመቻቾች ስልጠና ያግዝ ዘንድ የብዙኃን መገናኛዎችን መጠቀም፣

❖ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ላይ የአርብቶ አደሩን  የባለቤትነት ስሜት መገንባት

- ♦ የተቀናጀ ተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት የአርብቶ አደሩን ህይወት ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ በተመለከተ ግንዛቤ ማሳደግ።
- ♦ የጎልማሶች ትምህርት ጣቢያዎችን በማቋቋም በመቆጣጠርና በመምራት ረገድ የጎሳና የሀይማኖት መሪዎች ያላቸውን ተሳትፎ ማጎልበት፣

- የአርብቶ አደሩን ተወካዩች በማማከር ተገቢውን የጊዜ ሰሌዳ፣ አመቺውን ወቅት እንዲሁም፣ ተገቢውን የስርአተ ትምህርት ይዘትና የትምህርት መስጫ ስነዘዴዎችን መምረጥ፤
- ሴቶች በጎልማሶች ትምህርት እንደተማሪና እንደ ወደፊት አመቻች ሆነው በመርሀግብሩ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማስቻል ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ጋር መስራት፤

❖ ዘላቂነት ላለው የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማች ትምህርት አስተዳደር ተቋማዊ ስርአት መፍጠር::

- የግብርናና የገጠር ልማት፣ የአርብቶ አደር ልማት እንዲሁም የጤናና የሴቶች ጉዳይ መምሪያዎች የተጠናከረ ድርጅታዊ የግኙኙነት መዋቅር፣ አቅምና ትብብር እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ጣቢያዎችና ለመምራትና ለመደገፍ ይረዳ ዘንድ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ያለውን የጎልማሶች ትምህርት አመራርና አደረጃጀት ማሻሻል፣
- በአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ዘንድ ዘላቂነት ያለው የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራምን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማሰባሰብና ለማበልፀግ የሚረዱ ጠንካራ አጋርነቶችን ማጠናከር፣

❖ ለአርብቶ አደሩ የሚሰጠውን የጎልማሶች ትምህርት በተመለከተ ክትትልና ግምገማ ለመተግበር የሚያስችል ቀልጣፋ ድርጅታዊ መዋቅርና ስርአት መቅረፅ፣

- ሁሉንም ተዋንያን ያካተተና የጎልማሶችን የትምህርት መሻሻል የሚያሳዩ መለኪያዎችን ያካተተ ቀልጣፋ የጥራት ማረጋገጫ ስርአት መዘርጋት፣
- በክልል ቢሮዎችና በወረዳ ትምህርት ፅ/ቤቶች ውስጥ ግልፅ የስራ አመራር እንዲሁም የድጋፍና ክትትል መስጫ መዋቅሮችን መዘርጋት፣
- በጎልማሶች ላይ ያተኮረ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ በክልልና በወረዳ ደረጃ ማዋቀር፣ ከመስክ የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በመለዋየተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን ለማሻሻል

## ክፍል ሦስት ፡

### ዘርፈ-ብዙ ስትራቴጂያዊ ተግባራት

### 3.1. የትምህርት ጥራት ማሻሻያ

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *የሥርዓተ ትምህርት አግባብነት፣ የመምህራንና የአመቻቾችን የትም/ት ዝግጅት ዝግጅት በማሻሻል በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል፤*

በአርብቶ አደር አካባቢ በሚተገበረው ሥርዓተ ትምህርት የትምህርት ጥራትን ማሻሻልና ማረጋገጥ አለመቻል ዋናው ተግዳሮት ሲሆን የትምህርት ተቋማትም በጥልቅ ሲመረመሩ፤ክፍተቶች ይታይባቸዋል። ከነዚህም መካከል ዝቅተኛ የሆነ የትምህር ጥራት መኖር፣ የትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማት አለመሟላት፣ የመረጃ ስርአቱ አለመጠናከር፣ ያልተጠናከረ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት፣ እንዲሁም የትምህርት ቁሳቁሶችና የሰለጠኑ መምህራንና አመቻቾች እጥረት መኖር ናቸው።

የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ከሚያነሳቸው ቁልፍ ጉዳዮች ውስጥ የሥርዓተ ትምህርቱ ጥራት፣ አኗኗራቸውን ማለትም ማህበራዊ እሴቶቻቸውን፣ ባህላቸውን፣ አገር በቀል እውቀቶቻቸውንና ማህበራዊ መዋቅሮቻቸውን በማንፀባረቅ ረገድ ተገቢነቱ ውሱን መሆኑን ነው። የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታን የሚያሳይ የምርምር ማስረጃ በትምህርት ዘርፍ ውስጥ የማግኘትና የመጠቀም ውሱንነት የሚታይ ሲሆን በዚህም ምክንያት የትምህርት ጥራትን ከማሻሻልና ከማረጋገጥ አኳያ ሥርዓተ ትምህርቱ የአርብቶ አደሩን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ እንዳይሆን አድርጎታል።

ጥራት ያላቸው መምህራን ለትምህርት ጥራት ወሳኝ ቢሆኑም በውጤታማነትና በሙያ ብቃት የሚያገለግሉ መምህራን እና አመቻቾችን በነዚህ አካባቢዎች ማግኘት አዳጋች ነው። ከቅጥር ጀምሮ መምህራንን በስራ ላይ ማቆየትና ማልማትን በተመለከተ የአጠቃላይ የትምህርት ስርዓቱ ተግዳሮት ቢሆንም በአርብቶ አደር አካባቢ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ችግሩ የከፋ ነው።

የአርብቶ አደሩን የኑሮ ዘይቤ በአግባቡ የሚያውቁ ሆነው ወደ መምህራን ትምህርት ተቋማት ገብተው በመምህርነትና በአመቻችነት የሚሰለጥኑና የሚመረቁ በጣም አነስተኛ ናቸው።

በተጨማሪም መደበኛ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋ  በመምህርነት ወይም በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻችነት የመቀጠር ፍላጎት  የላቸውም።በተጨማሪም ተከታታይነት ያለውና በአግባቡ የታቀደ የመምህራን የስራ ላይ ስልጣና ዕድል ጠባብ ሲሆን  መሆንና አመቻቾችን ያካተተ  የደረጃ ዕድገት መሰላል ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። መምህራንን ከማዘጋጀትና ከማልማት አኳያ  የማሰልጠኛ ተቋማት ጠንካራ የትግበራ ድጋፍና በአካባቢው ሁኔታ የተቃኙ ፕሮግራሞችን ይሰጡ ዘንድ ብርቱ ትኩረት ይፈልጋሉ። የትምህርት ጥራትን ለማሻሻልና ለማረጋገጥ በተገቢው የሰለጠኑ፣ ብቃትና  ፍላጎት ያላቸውን መምህራን መቅጠርና በስራ ላይ ማቆየትን ይጠይቃል። በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት ለማሻሻል የሚከተሉት ስትራቴጂዎችና ተግባራት ይከናወናሉ፡-

- የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የመረጃ አስተዳደር ስረዓት መዘርጋት፣
- በአርብቶ አደር አካባቢዎች ላሉ የትምህርት ተቋማት ተስማሚ የሆኑ ስታንዳርዶች  እና መመዘኛዎችን (assessment) በመመስረት ተግባራዊ ማድረግ፤
- በስራ ላይ የሚገኙትን የትምህርት ተቋማት ስታንዳርዶች ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲያውቋቸው ማድረግ፤
- የትምህርት ጥራት ማሻሻያውንና የትምህርት ጥራት ማረጋገጫውን አስተዳደር የሚያስተጓጉሉ ክፍተቶችን ሊሞሉ የሚችሉ ስታንዳርዶችን ማዘጋጀት፤
- ብሄራዊ የት/ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በሚከተሉት መንገዶች መተግበር፣
    - የትምህርት ግብአቶች (መሰረተ ልማት ፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ፣ የመረጃና የኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች ፣ ወዘተ) እንዲሟሉ አስፈላጊውን ሁሉ ማከናወን፤
    - በሁሉም የትምህርት ተቋማት በቂ የመማር ማስተማር ቁሳቁሶች እንዲቀርቡ ማመቻቸት፤
    - የትምህርት ጥራት ሊጠበቅባቸው የሚችሉባቸውን ዘዴዎች (በጀት ምደባን ጨምሮ) መለየት፤
- የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የመምህራንና የአመቻቾች የመነሻ ቅጥርና የቀጣይ ሙያዊ ልማት እውን እንዲሆን የሥልጠናዎችን ጥራትና አግባብነት ማሻሻል፤
    - በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚሰሩ መምህራንና አመቻቾች የተለየ የደረጃ እድገት እርከኖችን ማስተዋወቅ፤
    - የመምህራንና አመቻቾች ቅጥርና መረጣን በተመለከተ ትኩረት መስጠት፤ መስጠት፣

- የአካባቢውን ቋንቋ የመናገር ችሎታ እንዲሁም ለአርብቶ አደር ልማት ያላቸው የቁርጠኝነት ደረጃ የ ቅጥር መስፈርት እንዲሆኑ ማካተት፤
- የአርብቶ አደር ትምህርት ባህሪያትን የተላበሰና የረጅም ጊዜ የሙያ እድገትን የተከተለ ልዩ የመምህራን ትምህርት ፕሮግራም መቅረፅ፤
- እያንዳንዱ መምህር የተሟላና በአግባቡ የተደራጀ የስልጠና ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆን ሁሉንም የስልጠና ክፍሎች በማቀናጀት ተቋማዊ አሰራርን መፍጠር፤
- መምህራንና አመቻቾች በልዩ ልዩ የሙያ እድገት መርሃ ግብሮች ማለትም በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ በሙያ መተዋወቂያ ኮርሶች እንዲሁም ፣ የሙያ ፍቃድና እድሳት ፕሮግራም ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል መፍጠር፤
- በአካባቢ ተመድበው ለሚሰሩ መምህራንና አመቻቾች የሚሰጠው የመደበኛ የስራ ላይ ሥልጠና ስለ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸውን እውቀት የሚያዳብሩበትና አስፈላጊውን ሙያዊ ክህሎት የሚያጎለብቱበት እንዲሆን ማስቻል፤

❖ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን በማዘጋጀትና በመተግበር ሌላ አካባቢ የሚሰሩ ውጤታማ መምህራንን ወደ አርብቶ አደሩ አካባቢ መጥተው እንዲሰሩ ማድረግ፤

❖ ተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ መቆየት፣ ውጤታቸውን መሻሻልና የሥርዓተ ትምህርቱን አግባብነት ማረጋገጥ፤

- አገር በቀል የአርብቶ አደር እውቀትን በሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ በማካተት እውቅና መስጠት፣
- በአንደኛ ደረጃ(1-6) ት/ቤቶች፣ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያናና በተንቀሳቃሽ ትም/ት ጣቢያዎች ትምህርትን በአፍ መፍቻ ቋንቋ መስጠትና የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች እንዲዘጋጁ ማድረግ፤
- ከአርብቶ አደሩ አካባቢ የአየር ሁኔታ፣ የእንቅስቃሴና ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ተለማጭ የትምህርት ካሌንደርና የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት
- ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት መለኪያዎችን በማዘጋጀ ለድጋፍና ክትትል ስራ መጠቀም እንዲሁም ስለሂደታዊ ምዘና ውጤታማነት መረጃ መስጠት፤

❖ የፍተሻ እንዲሁም የክትትል ግምገማ ተግባራትን ን ማጠናከር፤

- በክትትልና ግምገማ ሂደት ባለ ድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸው ሚና በተመለከተ ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

- ለሱፐርቫይዘሮችና ና የትምህርት አመራሮች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን፡፡ የመማር ማስተማር ሂደት ጥራትና በሥራ ላይ የዋሉ ስታንዳርዶች አተገባበር ለመከታተል ያመች ዘንድ አሳታፊ ዘዴዎችን መቀየስ፤

- የትምህርትን ጥራት የማሻሻልና የማረጋገጥ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ ተጨባጭ መረጃዎችን በጥናትና ምርምር መለየት ፤

## 3.2. የአርብቶ አደር ልጃገረዶች ትምህርት

ትራቴጂካዊ ዓላማ፡- *የአርብቶ አደር ልጃገረዶች የትምህርት ተሳተርፎን ማረጋገጥ*

- የትምህር ፍትሀዊነትን ዕውን ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ የሆኑ የአተገባበር ስልቶችና የትምህርት ግብአቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ የነዚህ መሟላት ትኩረትም እንደአጠቃላይ የአርብቶን ማህበረሰብ በተለይም የልጃገረዶችና የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ይሆናል፡፡ ሀገራዊ የልጃገረዶች ትምህርት ስትራተጂ የተዘጋጀ ሲሆን ስራ ላይ የሚገኙ ስትራተጊዎችንም ከአርብቶ አደሩ አካባቢያዊ ሁኔታ ጋራ አጣጥሞ በማዘጋጀት የሚተገበር ይሆናል፡፡ ከዚህም በላይ የልጃገረዶችን ትምህርት ለማጠናከር በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚከተሉት ስትራተጂዎችና ተግባራት ስራ ላይ ይውላሉ፡፡ ከባለድርሻ አካላት ፣ ከክልል ትምህርት ቢሮዎችና በትምህርት ዘርፍ ውስጥ ካሉ ሌሎች መዋቅሮች ጋር በመተባበር ለአርብቶ አደር ልጃገረዶች ትምህርትን ተደራሽና አመቺ ማድረግ፤

- ት/ቤቶችና የመማሪያ ማዕከላት በቂ ፣ አግባብነት ያላቸውና ለአርብቶ አደር ልጃገረዶች ተስማሚ የሆኑ አገልግሎት መስጫዎች እንዲሆኑ ማድርግ፤
  - ከቤት ወጥተው (በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፣ በከፊል አዳሪ ት/ቤቶችና በሆቴሎች ፣ ወ.ዘ.ተ ) መማር ለሚፈልጉ ልጃገረዶች ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ አገልግሎቱን እንዲያገኙ የሚያስችሉ ልዩና አዲስ አቀራረቦችን ማመቻቸትና መተግበር፤
  - ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ቅስቀሳዎችን በማካሄድ ማህበረሰቡ የልጃገረዶችን ትምህርት ጠቀሜታ በተመለከተ የግንዛቤ እንዲጨብጥና እንዲነሳሳ ማድረግ፤ ለልጃገረዶች ነፃ የትምህርት እድል በመስጠት ተሳትፎዋቸውንና ወደ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃዎች የመሸጋገር እድላቸውን ማስፋት፤
  - በት/ቤቶች የፆታ ክለቦችን በማቋቋም ለልጃገረዶች ልዩ የትምህርት ድጋፍ መስጠት፤

- በትምህርት ቤቶች የውሃ፣ የጽዳትና የግል ንፅህናማስጠበቂያ አገልግሎቶች ለልጃገረዶች ትምህርት ላይ መቆየት ካላቸው ጠቀሜታ አንጻር ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሟሉ መስራት፤ በማድረግ እነዚህ አገልግሎቶች ማረጋገጥ፡፡

### 3.3. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *በአርብቶ አደሩ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች ተሣትፎ ማረጋገጥ፣*

በትምህርት አገልግሎት እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች አካታች የሆነ የትምህርት አገልግሎት ላይ ማትኮር ያስፈልጋል። በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በብሔራዊ ደረጃ በተቀመጠው የአካታች ትምህርት ስትራቴጂ መሠረት ይስተናገዳሉ። በተጨማሪም የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ለማስፋፋት የሚከተሉት ስትራቴጂዎችና ሥራዎች ይተገበራሉ፡-

- ለውጤታማ እቅድ አወጣጥ መሠረት ለመጣል ይቻል ዘንድ በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በተመለከተ አስተማማኝ የመረጃ ቋት ማዳበር፣
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች ወደ ት/ቤቶችና የመማሪያ ማዕከላት ለማምጣና መገለልን ማስቀረት በተመለከተ አስፈላጊነቱ ላይ ለአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ፣ ለማህበረሰብ መሪዎችና ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ግንዘቤ ማስጨበጥ፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በሚገኙባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን መኖራቸውን ማረጋገጥ፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ቁሳቁሶች( የማዳመጫ ርዳ ፣ ማየት ለተሣናቸው ማንበቢያ፣ ተንቀሳቃሽ ወንበር፣ መነፅር፣ ወዘተ) ማሟላት፤
- |በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚገኙ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ሁኔታ ምላሽ የሚሰጥና ተለጣጭ የሆነ ሥርዓተ ትምህርትና የመማሪያ ቁሳቁስ ማዘጋጀት በእያንዳንዱ የመማሪያ ተቋምና ማዕከል ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ ምቹ የሆኑ መሰረተልማቶችና መሣሪያዎች እንዲደራጁ ማድረግ፣
- በልዩ ፍላጎት ትምህርት የተሸለሩና ተምሳሌት የሆኑ ሰዎችን በመለየትና በማስተባበር በት/ ቤቶችና በመማሪያ ጣቢያዎች የአመቻችነት ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ፣

- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ከሌሎቹ ከፍ ያለ የበጀትና ነፃ የትምህርት እድል ማመቻቸት፤

  የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን የማስተማር ፋይዳን በተመለከተ ተከታታይ የሆነ የማህበረሰብ ግንዛቤ በመፍጠር የነዚህን ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ የሚያስችል የድጋፍ ስራ ማካሄድ ።

### 3.4. የአደጋ ጊዜ ትምህርት

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጠው ትምህርት በአየር ለውጥ፣ በግጭቶችና በሌሎች የደህንነት ችግሮች ምክንያት የትምህርት አላስፈላጊ መስተጓጎል እንዳይደርስ መከላከል*

ኢትዮጵያ የትምህርትን ፍትሃዊ ተደራሽነት ልታረጋግጥ ካልቻለችባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በርካታ ልጆች በግጭት፣ በጦርነትና እንደ ጎርፍና ድርቅ በመሣሠሉት የአየር ለውጥ አደጋዎች ከትምህርት ቤት ውጪ በመሆናቸው ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል።የአርብቶ አደር አካባቢዎች እንደነዚህ ላሉ አደጋዎች የተጋለጡ በመሆናቸው ምክንያት በተለይም አደጋው በሚበዛባቸው ቦታዎች የተማሪዎች ቅበላ ዝቅተኛ ሲሆን መጠነ ማቋረጥም ከፍተኛ ነው። አግባብነት ያላቸው አካላት በአደጋ ጊዜ ምላሽ መስጠት ይችሉ ዘንድ የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ይተገበራሉ፤

- በአርብቶ አደር አካባቢዎችድንገተኛ አደጋዎች የሚያደርሱትን ጉዳቶች ለመፍታት በና የጋራ እርምጃዎች መውሰድ፤
- የድንገተኛ አደጋ መካከል እቅድን ለመደገፍ በቂ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ማዘጋጀትና በአካባቢው ስላሉ ድንገተኛ አደጋዎች መረጃ መስጠት፤
- ለትምህርት አመራር አካላትና ለማህበረሰቡ ስለ አደጋ ጊዜ ትምህርት ልዩ የአቅም ማዳበሪያ ስልጠና መስጠት
- መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱ ሲታወክ ስራቸውን እንዳያቋርጡ የሚያደርጋቸውን ጥልቅ ክህሎቶች ያዳብሩ ዘንድ ስለ አደጋ መቆጣጠር ፣ የአደጋ ሥጋት ቅነሣ፣ የስነልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ አሰጣጥ፣ የሠላም ትምህርትና ያታዊ ጥቃቅን በተመለከተ የተቀናጀ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- የአደጋ ጊዜ ትምህርትን በተመለከተ ትምህርታዊ ግንዛቤን በአርብቶ አደር አካባቢዎች ባሉ የመምህራን ሥልጠናዎች ውስጥ ማካተት፣

- ባህላዊ የግጭት አፈታትና በሠላም አብሮ የመኖር ጥረቶችን ከመደገፍ አኳያ ትምህርት ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤
- የአርብቶ አደር አካባቢ የትምህርት ተቋማትን በተመለከተ የሚመለከታቸው ሴክተሮችናዘርፎች የአደጋ ዝግጁነት ምላሽ እቅድ ማዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣
- የአደጋ ጊዜ ትምህርትን በተመለከተ ዝቅተኛው የትምህርት ስታንዳርድ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በድርቅና በሌሎች ችግሮች የተጎዱ ተማሪዎችን የሚቀበሉ ትምህርት ቤቶችን በማዘጋጀት ረገድ በአጎራባች ክልሎችና ትምህርት ቤቶች መካከል ትብብር እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- በአርብቶ አደር አካባቢዎች የትምህርት ቤት ምገባ ሥርዓቶች (School feeding) እንዲጠናከሩ ማድረግ።

### 3.5. የትምህርት አመራርና አስተዳደር አቅም ግንባታ

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *ለአርብቶ አደር ማህበረሰብ ነባራዊ ሁኔታ በቂ ምላሽ እንዲሰጡ ለማስቻልና የፖሊሲና መመሪያዎች አተገባር ውጤታማነት ቀጣይ እንዲሆን ማድረግ እንዲቻል የትምህርት አመራር አካላትን የማስፈፀም አቅም ማሻሻል*

የትምህርት አገልግሎት አሰጣጡ ከየአካባው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲሄድ ለማስቻል ሀገራዊው የትምህርት አስተዳደር የፖሊሲ ማዕቀፍ ላልተማከለው የትምህርት አመራር ሰፊ የስራ ድርሻ ሰጥቶታል። በአርብቶ አደር አካባቢ በእያንድንዱ እርከን ያለው ያልተማከለ የትምህርት አስተዳደር ስርአት በሙሉ አቅሙ እንዲሰሩና የየራሳቸው ግልፅ ሚና ሊኖራቸው ይገባል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የመረጃ ፍሰቱ ወጥነት የጎደለውና ለሚከናወኑ ተግባራትም ቢሆን ያልተሟላ መረጃ የሚቀርብበት ነው።

የሰራተኞች ስራ ገበታ ላይ አለመቆየት ጠንከር ያለ አመራር መመስረት እንዳይቻል በማድረጉ ይህም ክፍተት ተቋማዊ መረጃን ለመያዝም ሆነ ምን እንደተሞከረ ምን ውጤታማ እንደሆነ እና እንዳልሆነ እንዲሁም የእነዚህን ምክንያቶች ለማወቅ እጅግ አስቸጋሪ አድርጎታል። ባልተማከለው የትምህርት ስርአት በትምህርት ቤት ፣ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ የተሻለ የፖሊሲና እስትራቴጂ አፈፃፀም ማምጣት ይቻል ዘንድ የስራ አመራር አቅም ግንባታን ማጠናከር ያስፈልጋል። ለተፈጠረው ሰፊ የአፈፃፀም ክፍተት ምክንያቱ የበጀት እጥረት እንደሆነ በሁሉም ደረጃዎች ባሉ ኃላፊዎች በስፋት ይታመናል። ይህ በግልፅ የሚታይ ችግር ቢሆንም የተመደበውን በጀት በአግባቡ የመጠቀም አቅምንም ማጠናከር ያስፈልጋል።

በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለውን የትምህርት ስራ አመራር አቅም ለማሻሻል የሚከተሉት ስትራቴጂዎችና ተግባራት ይከናወናሉ።

- በአርብቶ አደር አካባቢ የሚገኙ የትምህር ተቋማት፣ የአደረጃጀት መዋቅሮች እንዲሁም የትምህርት አመራርና አስተዳደር አካላትን በማጠናከር ግልፅ ስትራቴጂ፣ ራዕይና ዓላማ ኖራቸው ጥራት ያለውን ትምህርት መስጠት እንዲችሉ አቅማቸውን ማሻሻል፤
- የትምህርት ስራ አመራር አካላትን፣ ኤክስፐርቶችንና ዕቅድ ባለሙያዎችን በውድድር፣ ብቃትና የትምህርት ዝግጅት፣ ላይ በተመሰረተ የቅጥር ሂደት ብቻ ለኃላፊነት ማብቃት፤
- የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች የቁጥጥርና የድጋፍ ስራዎች ማጠናከር፤
- ጠንካራና ወጥነት ያለው የመረጃ አደረጃጀት ስርአትን መዘርጋት፤
- በእያንዳንዱ የመዋቅር እርከን ላይ ላሉ የትምህርት ባለሙያዎች ግልፅ ኃላፊነቶችንና ተጠያቂነቶችን ማስቀመጥ፣
- በትምህርት ቤቶች እና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት የአመራሮች ተሳትፎን ለማሻሻል ስልት መንደፍ፤
- ለትምህርት ስራ አመራር አካላት የሙያ ማሻሻያ እድሎችን ማቅረብ፣፤
- ከስራ ላይ መቅረትን ለመቀነስ የመምህራንና የአመቻቾችን ደመወዝ በወቅቱ መክፈል፣፤
- አግባብነት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ግልፅነትና አሳታፊ የውሳኔ አሰጣጥና ፍትሀዊ አስተዳደር እንዲኖር ማስቻል፤
- ግብአቶችን በውጤታማነትና በቅልጥፍና የመጠቀም አቅምን ማጠናከር፤
- አግባብነትና ቀጣይነት ያላቸው የቅስቀሳና ግንዛቤ መፍጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተሳትፎ ያልነበራቸውን የግል ዘርፎች ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻዎችን በማካተት ለአርብቶ አደር ትምህርት የገንዘብ ድጋፍና አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማበረታታት።

### 3.6. የፋይናንስ አሰባሰብና አጠቃቀም

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *የገንዘብ አጠቃቀሙ እስትራተጂውን ለመተግበር በሚያስችልና ውጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ።*

የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ የትምህርት አገልግሎት በስትራቴጂው መሰረት እንዲስፋፋ ከተፈለገ ትግበራው በበቂ በጀት ሊደገፍ ይገባል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ሁሉም ባለድርሻ

አካላትና የክልል ትምህርት ቢሮዎች ቋሚ የፋይናንስ ምንጮችን ከማመቻቸት ጎን ለጎን ሀብት የማፈላለግ፣ የተገኘውን በአግባቡ ስራ ላይ የማዋልና የተጠያቂነት መርህን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የሚከተሉት ስትራቴጂዎችና ስራዎች የገንዘብ ሀብት አጠቃቀምን ለማሻሻል ይተገበራሉ።

- የሀብት አሰባሰብ ስትራቴጂን በመንደፍ ድጋፍን ከለጋሾችና ከልማት አጋሮች በማሰባሰብ የመንግስትን ጥረቶች መደገፍ፤
- ወቅቱን የጠበቀ የሀብት ስርጭት ከማድረግ አንጻር ሊኖሩ የሚችሉ እንቅፋቶችን አስቀድሞ በመለየት ማስወገድ፤
- ከራሱ ከማህበረሰቡና ከልማት አጋሮች ድጋፍ በማሰባሰብ የአርብቶ አደር የትምህርት ፈንድ መመስረት፤
- የትምህርት ስራውን የሚመሩ አካላት አቅም በመገንባት የገንዘብ አስተዳደርና አጠቃቀምን ማሻሻል፤
- የበጀት ክትትልና ግምገማ ስርአት መዘርጋት።

### 3.7. የአጋርነት ስራ ለትምህርት ልማት

**ስትራቴጂያዊ ዓላማ፡-** *አሳታፊና ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ አጠቃላይ ማዕቀፎችን በመገንባት በአለም አቀፍ፣ በብሔራዊ፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ እንዲሁም በማህበረሰብ ደረጃ በአግባቡ የተጣመሩ ምርታማና ግልፅነት ያላቸው ብዝሀዊ አጋርነቶችን መመስረት*

ሀገራዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂም ሆነ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ስትራቴጂያዊ ዕቅዶች አተገባር የሁሉንም ባለ ድርሻ አካላት ርብርብ ይጠይቃል። እነዚህ ባለድርሻ አካላትም የልማት አጋሮች ፣ ለጋሾች ፣ ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ፣ የትምህርት ተቋማት ፣ ተመራማሪዎችና መምህራንን ያካተቱ ናቸው። አጋርነት መመስረት ማለት የጋራ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች እውቀት ፣ መረጃና ግብዓቶችን ለመጋራት እንዲቻል ለረጅም ጊዜ የሚፈጥሩት ትብብር ነው።

መሰረተ ልማቶችና የትምህርት ቁሳቁሶች በማሟላት፣ለአመቻች ስልጠና አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን በማቅረብ አጋሮች ጠቃሚ ሚና መጫወታቸውን ይቀጥላሉ። ዕቅዶችን በጋራ ማዘጋጀት መጠናከርና ይህም በተጠናከረና የጋራ መተማመንን መሰረት ባደረገ መልኩ ግንኙነቶችን መመስረት ይጠይቃል። ውጤታማነትን ለማሻሻል በመንግስት፣ መንግስታዊ

ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በአርብቶ አደር ጎሳዎችና አመራሮቻቸው መካከል የተቀናጀና አወንታዊ አጋርነትን መፍጠር ያስፈልጋል።እርስ በእርስ የመተማመን ስሜትን መፍጠር አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ የስትራቴጂውን አፈፃፀም ማሻሻል ይቻል ዘንድ መንግስት የማህበረሰቡ ባህላዊ አደረጃጀቶችን መጠቀም ይገባዋል።በአርብቶ አደር ማህበረሰብ አካባቢ የትምህርት ልማትን ለመስፋፋትና ለማሻሻል የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ ተግባራት ይከናወናሉ ።

- አጋርነቶችን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ አቅሞችና ብቃቶችን መለየት፣
  - ባለ ድርሻ አካላትን እንደ ትኩረታቸው እና አቅማቸው የመመደብ ስራን መስራት ፣ በስራ ላይ ያሉ ሙያዊ ስልቶችን መጠቀምና በአርብቶ አደር ትምህርት ላይ የሚሳተፉትን የመንግስት ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና ሌሎች የልማት አጋሮችን ማጠናከር
  - ሌሎች አስተዋጾ ለማድረግ አቅሙና ፍላጎቱ ያላቸውን አካላት መለየት።
- አሳታፊና ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ የአጋርነትና ትስስር ስርዓትን አጠቃላይ ማዕቀፍ ማደራጀት፣
  - ወርክሾፖችና የውይይት ፎረሞችን በማዘጋጀት ከአርብቶ አደር ትምህርት ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ የስራ ሀላፊነቶችን ዝርዝር መወሰን፣
  - የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂን በውጤታማነት መተግበር ይቻል ዘንድ ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት ድጋፍና ትብብር እንዲኖራቸው ማንቀሳቀስ ማንቃትና ማሰማራት፣
  - በመንግስትና በግል እንዲሁም በሲቪል ማህበረሰቦች መካከል የአጋርነትና የትስስር ስትራቴጂዎች መንደፍ፣
  - የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላትን ሚና በግልፅ ማስቀመጥና ጥንካሬዎችን ማጉላት፣
  - በስራ ላይ ያለውን የአርብቶ አደርና የአጎራባች ክልሎች ትብብር ማስቀጠልና በሁሉም የትምህርት ስርዓት ንዑስ ዘርፎች ላይ ያለውን ትብብር ወደተሻለ ደረጃ ማሳደግ፣
- አግባብ ካላቸው ዩንቨርሲቲዎችና ሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ትምህርት ለአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ በሚስፋፋበት ሁኔታ ላይ ምርምር እንዲደረግ ማገዝ
  - በመምህራን ልማትና በስርአተ ትምህርት ክለሳ እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ የመማር ማስተማር ግብዓቶች ማዘጋጀትን በተመለከተና ውጤታማነት የሚያሻሽሉ ግምገማዎችን በአርብቶ አደር አካባቢ ካሉ ዩንቨርሲቲዎች ጋር አጋርነትን በመፍጠር ፈጠራ በተሞላበት መልኩ ማበልፀግ፣

- ክልላዊ፣ አካባቢያዊና አለማቀፋዊ አጋርነቶችን ማደራጀት፣
  - ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍን ማሰባሰብ ይቻል ዘንድ በአለም አቀፍ ደረጃ አግባብነት ካላቸው የምርምርና የትምህርት ተቋማት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች እንዲሁም ከመንግስት ጋር የሁለትዮሽ ትብብር ካላቸው አካላትና በጎ አድራጊ ግለሰቦች ጋር ትስስር መፍጠር፤
  - ዓለም አቀፍ አጋርነቶችና ትስስሮች በመመስረት የአርብቶ አደር ትምህርትን ከሚተገብሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ልምድ መቅሰም፤
  - ድንበር ዘለል የትብብር አጋርነት ስትራቴጂዎችን በማጠናከር በአገራት ድንበሮች መካከል የሚንቀሳቀሱ አርብቶ አደሮች ፍላጎት ማሟላት፤
  - የተቀናጀ የትምህርት ልማትን ማስፈን ይቻል ዘንድ አካባቢያዊና ክልላዊ የጉርብትና አጋርነቶችን ማጠናከር።
- ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ጋር አጋርነትን ማጠናከር፡- ይህም
  - በአርብቶ አደር ማህበረሰብና በትምህርት ማዕከላት መካከል ያለውን አጋርነት ማጠናከር፤
  - ት/ቤቶችን፣ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች፣ የህፃናት እንክባካቤና ትምህርት ማዕከላት፣ ተንቀሳቃሽየአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ፣ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ማእከላትና ሌሎች የመንግስት አካላትን ኃላፊነቶችን በተመለከተ የስራ ድርሻቸውን እንዲረዱ ለማህበረሰብ ተወካዮች ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
  - አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ የትምህርት ፋይዳን እንዲረዳና መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈስ በልዩ ልዩ መንገዶች ማለትም የማህበረሰብ ተወካዮች፣ የማህበረሰብ ሬዲዮኖችን፣ የሬዲዮ አድማጭ ቡድኖችንና ሌሎች መንገዶችን በአግባቡ መጠቀም ፤
  - ስለ ዓለማዊ ትምህርት አስፈላጊነት እንዲሁም የትምህርት ተሳትፎ ስለሚገድቡ ባህላዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ማለትም የፆታ ልዩነት ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻና፣ የህፃናት ጎልበት ብዝበዛ የመሳሰሉት ላይ የአርብቶ አደሩን ግንዛቤ ማሳደግ፣
  - ማህበረሰቡ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆችና ልጃገረዶችን ወደ ት/ቤቶችና የመማሪያ ማዕከላት እንዲልክና እንዲስተምር ግንዛቤውን ማሳደግ፣

- ከአካል ጉዳት ጋር የተያያዙ ማግለሎችን ለማስቀረት የተደራጀ የህዝብ የግንዛቤ ቅስቀሳ ስራዎችን ማካሄድ፣

### 3.8. የተማሪዎች የምዘና ሥርዓት

ተከታታይ ምዘና አንዱ የምዘና ዘዴ ሲሆን አመቻቾችና መምህራን የተማሪዎችን እውቀት፣ክህሎትና አመለካከት ለመመዘን የሚጠቀምበት መሳሪያ ነው። በተጨማሪም በሁሉም የትምህርት አቀራረብ ስልቶች ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ ነው።የሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እንደሚያሳው ክልላዊና አገራዊ ፈተናዎች የሚሰጡት ስድስተኛ፤ስምንተኛና 12ኛ ክፍሎች መጨረሻ ላይ ነው። በመሆኑም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተማሪዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርትክልላዊ ፈተና የሚወስዱት የደረጃ ስድስት ትምህርትን ሲያጠናቅቁ ይሆናል። የዚህን ደረጃ ትምህርት በውጤታማነት ካጠናቀቁ በኋላ የመካከለኛ ደረጃ ትምህትን በመከታተል ለስምንተኛ ክፍል ፈተና ይዘጋጃሉ።የስምንተኛ ክፍል ፈተና ስታንዳርድ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ በክልል ደረጃ የሚሰጥ ሲሆን በመካከለኛ ደረጃ የሚተገበረው ሥርአተ ትምህርት ተመሳሳይ በመሆኑና ተማሪዎችበአገር አቀፍ ደረጃ ሊኖር የሚገባውን አጥጋቢ የትምህርት የብቃት ደረጃ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ነው።

በተመሳሳይ የ12ኛ ክፍል መጨረሻ ፈተና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው ሥርአተ ትምህርቱ ተመሳሳይ በመሆኑና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ ተማሪዎች የቀሰሙትን የዕውቀትና የክህሎት ደረጃ ለማወቅ፣ ለከፍተኛ ትምህርት ያላቸውን የዝግጅት ደረጃ ለመረዳትና ፈተናውን በበቂ ሁኔታ ያለፉትን የከፍተኛ ትምህርት እንዲከታተሉ ለማድረግ ነው።

# ክፍል አራት፡

## ስትራቴጅያዊ ተግባራትና የፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 4.1. ስትራቴጅያዊ ተግባራት

የስትራቴጂውን ዓላማዎች ለማሳካት በመላው የትምህርት ስርአቱ ውስጥ የባለቤትነት ስሜትን ማሳደግና ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል። ስትራቴጂው የሚጠይቀውን መረዳትና መንፈሰ ጠንካራነት እንዲሁም ዘለቄታዊነት ያለው ግንኙነት ከአጋር አካላት ይተበቃል። ለአርብቶ አደር ትምህርት የሁኔታ ትንተና ከመረጃ ሰጪ አካላት የተገኘው ግብዓት የለውጥን አስፈላጊነትና ከማሳየቱም በላይ የወደፊት አቅጣጫን በማሳየትና ለግንዛቤ መፍጠሪያነት ጥቅም ላይ ውሏል። ከቁልፍ የመረጃ ሰጪ አካላት የተገኙት ሃሳቦች በክፍል ሁለት ውስጥ በቀረቡት ምክረ ሀሳቦች ፣ ዓላማዎችና ስትራቴጂካዊ ተግባራት ውስጥ በሰፊው እንዲካተቱ ተደርጓል። ያልተማከለው የትምህርት አመራር ስርዓት የትምህርት ግብአቶችንና አገር በቀል እውቀቶችን በቅርበት ለመጠቀም ስለሚያስችል ለስትራቴጂው ትግበራ አመቺ ነው። ሆኖም በተለያዩ እርከኖች ያሉ የመንግስት መዋቅሮች እርስ በእርስ ተሳስረውና ተደጋግፈው በመስራት መጠናከር ይገባቸዋል።

ቀጣዩ ተግባር ከአርብቶ አደር ትምህርት አኳያ ልዩ ልዩ የትምህርት መዋቅሮች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚናዎችንና ኃላፊነቶችን መለየት፣ የትምህርት ማቅረቢያ ስርአቶችን መተግበርና የመፈጸም አቅም ፍላጎቶችን መመዘን ይሆናል።

## 4.2. የፈጻሚና የአጋር አካላት ተግባርና ሃላፊነት

### 4.2.1.ትምህርት ሚኒስቴር

የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር የተለያዩ ሀገር አቀፋዊ ስትራቴጂዎችን መከለስና ሌሎች የማስፈፀሚያ ሰነዶችን ማዘጋጀት፤ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን መገንባት እንዲሁም የክትትልና ግማገማ ስራዎችን በማስተባበር የማስፈፀም ስራ ይሰራል። በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ልዩ ድጋፍ ለአርብቶ አደር አካባቢዎች የመስጠቱን ሚና የሚቀጥል ሲሆን ለአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጠው ድጋፍም ስራቸውን በራሳቸው አቅም መተግበር እስኪችሉ ድረስ የሚቀጥል ሲሆን የጋራ እቅድ በማውጣት የክትትልና ግምገማ ስርአቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል።

ለትምህርት ስርአቱ መተግበር ከተቀመጡለት የስራ መዘርዝሮች በተጨማሪ ከአርብቶ አደር ትምህርት አኳያ ትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ቁልፍ ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

- በልዩ ልዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች መካከል ያሉትን ጥምረቶችና ትስስሮች በማጠናከር የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ትምህርት ለማሻሻል። የአርብቶ አደር የትምህርት ስትራቴጂ ከሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ተግባራት ጋር እንዲቀናጅ በማድረግና የአርብቶ አደሩን ህይወት ለማሻሻል ከሚደረጉ መጠነ ሰፊ የልማት ጥረቶች አኳያ እንዲተገበር የመሪነት ሚናውን መጫወት አለበት፣
- ከአርብቶ አደር ትምህርት አኳያ በብሔራዊና በክልል ደረጃ ለሚገኙ ቁልፍ የባለ ድርሻ አካላት የስራ ድርሻና ኃላፊነቶችን በግልፅ ማስቀመጥ፣
- ለአርብቶ አደር አካባቢዎች የትምህርት ስታንዳርዶችን ማዘጋጀት፣ መልካም ተሞክሮዎችን ማሰባሰብ፣ ማጠናቀርና እውቀትን ማሰራጨት።
- የአርብቶ አደር የትምህርት ፕሮግራሞችን ከልዩ ልዩ የባለድርሻ አካላት የትግበራ እቅድ ጋር የተሳለጡ ለማድረግ የጋራ እቅድን ማውጣት፣ እንዲሁም የክለሳና ግምገማ ስብሰባዎችን ማካሄድና በሰነድነት መያዝ፣
- የገንዘብና የሰው ሃብትን ለውጤታማ የስራ አመራር መዳበር፣ ለተሻለ ቅንጅታዊ አሰራርና አጋርነት በመጠቀም የአርብቶ አደር ትምህርትን በሁሉም ደረጃዎች ማሻሻል።
- በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የትምህርት አመራር አካላት ተግባርና ኃላፊነቶች ግልፅነትንና ተጠያቂነትን የተላበሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

- ቁልፍ የስራ አፈፃፀም አመላካቾችን በመጠቀም መደበኛ (ዓመታዊ) የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በማከናወን አቅምን መገንባት። ለዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ለቁልፍ የስራ አፈፃጸም አመላካቾች ስታንዳርዱን የጠበቀ የመከታታያ ቼክሊስትና ዝርዝር ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን ማዘጋጀት፣
- ለአርብቶ አደር አካባቢዎች የአርብቶ አደር ትምህርት ልማት ፍኖተ ካርታና ማስተር ፕላን ማዘጋጀት፣
- ብሄራዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ምክር ቤት መመስረት፣
- ለህፃናት እንክብካቤና ትምህርት፣ ለተንቀሳቃሽ ትምህርት እንዲሁም ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ብሔራዊ ዓብይና የቴክኒክ ኮሚቴ መመስረትና ማጠናከር።
- የአርብቶ አደር ትምህርት የግብአት ማእከልን ማቋቋም።
- ብሔራዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ኮንፈረንስን በየዓመቱ ማዘጋጀት።

### 4.2.2.የክልል ትምህርት ቢሮዎች

በአርብቶ አደር አካባቢች ያሉ ክልል ትምህርት ቢሮዎችና የዞን ትምህርት መምሪያዎች በአርብቶ አደር የትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ለትምህርት ስርአቱ ትግበራ ከተቀመጡለት የስራ ኃላፊነቶችና ተግባራት በተጨማሪ እያንዳንዱ ክልል ትምህርት ቢሮ የራሱን የአካባቢውን ሁኔታ መሰረት ያደረገ ዘዴ በመጠቀም የሚከተሉትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይወጣል።

- በክልሉ ውስጥ ያሉ አርብቶ አደር ልጆች ትምህርትን በተመለከተ ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን እንዲሁም ክፍተቶቹን ይለያል።
- ሀገራዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂን በሚደግፍና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ ሁኔታ ግልፅ ራዕይና ተልዕኮ ያለው የአርብቶ አደር ትምህርትን የሚያስፋፉ ክልላዊ የስትራቴጂ ዕቅድ ማዘጋጀት። የክልላዊ ስትራቴጂያዊ ዕቅዱም፡
    - አግባብነት ያላቸው የትምህርት አቅርቦት ስልቶችና ስትራቴጂዎችን ለክልሉና በውስጡ ላሉት ወረዳዎች ይመርጣል።
    - ኢላማዎችን፣ ተግባራትን፣ የጊዜ ማዕቀፎችን፣ የአፈፃፀም እርምጃዎችንና አመላካቾችን በግልፅ የሚያሳዩ ዓላማዎችን ይለያል ።

- ክልል አቀፍ የማስተግበሪያ እቅድና የአፈጻጸም መምሪያ በማዘጋጀት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።
  - የሚመለከታቸውን የትምህርት አመራር አካላትን፣ ፈፃሚዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ ተባባሪዎችን, የልማት አጋር አካላትን ተሳትፎ ደረጃ የማሳደግ።
  - የእያንዳንዱን ተባባሪ አካል ጠንካራ ጎኖች በይበልጥ መጠቀም ይቻል ዘንድ ለእያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት ግልፅ ኃላፊነቶችን የመስጠት።
  - እስከታችኛው እርከን ባሉ መዋቅሮች የሚስተዋሉ የአቅም ክፍተቶችንና የሚፈለጉ ፕሮግራሞችን በመለየት የመፈፀም አቅምን በመገንባት ስትራቴጂው ስኬታማ የማድረግ
- የገንዘብና የሰው ሀብት ምንጭን ማሻሻል፣
  - በክልል ደረጃ የገንዘብ ማሰባሰብ ስትራቴጂዎችን መንደፍ፣ አግባብነት ያላቸውን ባለድርሻ አካላትንና የገንዘብ ምንጮችን መለየት፣
  - ለስትራቴጂው ትግበራ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ማካሄድ
  - ለአርብቶ አደር ትምህርት የዞን መዋቅሮችንና የስራ አመራርን ማጠናከር
  - በአርብቶ አደር አካባቢዎች በትምህርት ስራ ሊሰማሩ የሚችሉ ባለሙያዎችን ሊስቡ የሚችሉ የማበረታቻ ስልቶችን መንደፍና መተግበር፣
- የትምህርት ግብአቶችን ድጋፍ ማቅረብ፡-
  - በብሄራዊ የስራ መመሪያዎችና ማዕቀፎች መሰረት ለመደበኛና መደበኛ ላልሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚውል አግባብነት ያላቸውና ስርአተ ትምህርትና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለአርብቶ አደር አካባቢ ማዘጋጀትና ማሰራጨት።
  - የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ቁሳቁሶችን በመደበኛ ትምህርት ቤቶችና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ማቅረብ።
- የመረጃና የግንኙነት አስተዳደሩን ማሻሻል፡
  - ውጤታማ የመረጃ አደረጃጀት ስርዓት መቅረፅና መተግበር።
  - በአፈፃፀም መለኪያዎችና አመላካቾች መሰረት የክትትልና ግምገማ ስርአት መዘርጋት።
  - በክልሉ ለአርብቶ አደሮች ትምህርት የሚያስፈልገውን ልዩ ድጋፍ መለየትና እነዚህን ፍላጎቶችንና መሻሻሎችን በወቅቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ማሳወቅ። እንደ ክልላዊ ማዕከል በማገልገል የአርብቶ አደር ትምህርትን ማስተዋወቅ የአርብቶ አደር ልጃገረዶች፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች እና ሴት መምህራንና አመቻቾች

እንዲሁም ሴት የትምህርት አመራሮች፣ በትምህርቱ ሥራ ላይ አግባብ ያለው ተሳትፎ ያደርጉ ዘንድ አዎንታዊ ድጋፍ ማድረግ።

- ከልማት አጋር ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር ትስስርን፣ የግንኙነት መረብንና አጋርነትን መዘርጋትበአርብቶ አደር ትምህርት ስራ ከተሰማሩ አጋሮችና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚካሄደውን የክትትልና ግምገማ ስራ ማስተባበርና የጋራ ተግባራትና ኃላፊነቶች ፍሬያማ እንዲሆኑ ማበረታታት
- ክልላዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ኮንፈረንሶችን በማዘጋጀት የመልካም ተሞክሮ ልውውጥ መድረኮችን መፍጠር፣
- ለህፃናት እንክብካቤና ትምህርት እና ለተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የክልል ምክር ቤቶችን ማቋቋም እነደዚሁም ለተንቀሳቃሽ ት/ቤቶችና ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ታቢያዎች ደረጃ ማሳደጊያ የቴክኒክና አስተባባሪ ኮሚቴዎችን መመስረት፣
- ለአርብቶ አደር አካባቢዎች የመምህራን ትምህርት ፕሮግራም ክልላዊ ማስተር ፕላን ማዘጋጀት፣
- የአርብቶ አደር ሴቶች ትምህርት ፎረሞችን መመስረት፣
- ለተሻለ እቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ያመች ዘንድ ክልላዊ የትምህርት ምዘናና ግምገማን ማከናወን፣

### 4.2.3.የዞን ትምህርት መምሪያዎች

በትምህርት ስርአቱ ውስጥ ከተቀመጡት የስራ ድርሻዎቹ በተጨማሪ ከአርብቶ አደር የትምህርት ስትራቴጂ አፈፃፀም አኳያ የዞን ትምህርት መምሪያ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡

- የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂን ለመተግበር ከክልል ትምህርት ቢሮ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ መስራት፣
- የስትራቴጂውን ትግበራ ማረጋገጥና በዞኑ ስር ላሉ ወረዳዎች የሱፐርቪዥን ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣
- ከክልል ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር ተፈላጊ የትምህርት መገልገያዎችና መሳሪያዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ።
- ለአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ውጤታማ ትግበራ ያመች ዘንድ ከክልል ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር አጫጭር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፣

- በዞኑ ውስጥ ያሉ የአርብቶ አደር ልጆችና ጎልማሶችን የትምህርት ተደራሽነት እና ተሳትፎ የሚያሳይ መረጃን ማሰባሰብና የተገኘውን መረጃ ለክልል ትምህርት ቢሮ ማሳወቅ፣
- ዓመታዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ኮንፈረንስ ማዘጋጀት፣
- በዞን ደረጃ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት የውይይት ፎረም ማቋቋም፣
- በአርብቶ አደር ትምህርት ላይ ዓመታዊ የስራ ግምገማ ስብሰባዎችንና ውይይቶችን ማካሄድ፣

### 4.2.4.የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት

የስትራተጂውን አፈፃፀም በሚመለከት የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ቀዳሚ ሚናዎች ከክልል ትምህርት ቢሮ ጋር በሚደረግ የቅርብ ምክክር ይለያሉ። በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ከተቀመጡለት ድርሻዎች በተጨማሪ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ከአርብቶ አደር ትምህርት የትግበራ ስትራቴጂ አኳያ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

- የክልሉን የስትራቴጂ ዕቅድ ወደታች ማውረድና የእቅድ ክንውኖችንና ተዛማጅ ድርጊቶችን የመፈፀም፣ የመከታተል፣ የመቆጣጠርና የመገምገም ኃላፊነትን መወጣት።
- ከዞን ትምህርት መምሪያ፣ ከክልል ትምህርት ቢሮና ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር ከመፈጸም አቅም፣ ከስራ አፈጻጸም ፣ ከስርአተ ትምህርት ይዘት፣ ከመምህራን/ አመቻቾች ምደባና ጥራት አኳያ የወረዳውን ፍላጎት ለክልል ትምህርት ቢሮ ማማከር፣
- በዞን ትምህርት መምሪያና በክልል ትምህርት ቢሮ ድጋፍ አግባብ ያለው የመረጃ አደረጃጀት ስርዓት መመስረትና መተግበር፣
- በወረዳው ውስጥ የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ዓላማዎችን ዕውን ለማድረግ የወረዳውን የትምህርት አጋር አካላት ትብብር ውጤታማ ማድርግ።
- ስትራቴጂውንና የእቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ ለአካባቢው ማህበረሰብ፣ ለጎሳ መሪዎች፣ ለጣቢያ ስራ አመራር ኮሚቴዎች፣ ለቀበሌ አስተዳደር፣ ተፅኖ ፈጣሪ የማህበረሰቡ ተወካዮች የግንዛቤ መፍጠሪያ ፎረሞችን ማዘጋጀት፣
- ለፈፃሚዎችና ለትምህርት ስራ አመራሮች የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣
- በስትራቴጂው አተገባበር ላይ በተቀናጀ ሁኔታ የቁጥጥር የክትትልና ግምገማ ስራዎችን በተደጋጋሚ ማከናወን፣
- ለህፃናት እንክብካቤና ትምህርት፣ ለተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶችና ለተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት /inter-sectoral/ በተቋማት መካከል የተቀናጀ የቴክኒክ

ኮሚቴዎች መመስርት እንዲሁም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ደረጃ ለማሳደግ አብይ ኮሚቴ መመስረት፣

- አዳዲስ ት/ቤቶችና ሌሎች የትምህርት ማዕከላት ስለሚገነቡበት አስተያየት ማቅረብ፣
- የዞን መዋቅር በሌሉባቸው አካባቢዎች የዞን ትምህርት መምሪያ ተግባራትን በማከናወን ኃላፊነቶችን መወጣት፣

### 4.2.5.የጉድኝት ማዕከላት

የስትራቴጂውን ትግበራ ለማገዝ የጉድኝት ማዕከላት ተጠናክረው የሚከተሉትን እንዲያከናውኑ ይደረጋል።

- ለመምህራንና ለአመቻቾች ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣
- ለት/ቤቶችና ለመማሪያ ማዕከላት ተገቢነት ያላቸው ቁሳቁሶችንና ግብዓቶችን ማቅረብ።
- ለት/ቤቶችና ለመማሪያ ማእከላት የሱፐርቪዥን ድጋፍ መስጠት፣
- በወቅታዊ የትምህርት አሰጣጥ እና ምዘና ዘዴዎች ስልጠናዎችን መስጠት፣
- በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች እንዴት ማዘጋጀትና መጠቀም እንደሚቻል ለመምህራን እና አመቻቾች ስልጠና መስጠት፣
- ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራንና አመቻቾች የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- በጉድኝት ማዕከላት ደረጃ የትምህርት ምዘናና የማጠቃለያ ፈተና በማዘጋጀት መስጠት፣

### 4.2.6.ትምህርት ቤቶች /ጣቢያዎች/

የስትራቴጂውን ትግበራ ለማገዝ ት/ቤቶች ተጠናክረው የሚከተሉትን እንዲያከናውኑ ይደረጋል።

- ለመምህራንና ለአመቻቾች ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣
- ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃና የትምህርት ዓይነቶች ተገቢነት ያላቸው ቁሳቁሶችንና ግብዓቶችን ማቅረብ፣
- ለመምህሩ የክፍል ውስጥ ሙያዊ የሱፐርቪዥን ድጋፍ መስጠት፣
- በወቅታዊ የትምህርት አሰጣጥ እና ምዘና ዘዴዎች ስልጠናዎችን መስጠት፣
- በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች እንዴት ማዘጋጀትና መጠቀም እንደሚቻል ለመምህራን እና አመቻቾች ስልጠና መስጠት፣

- ለመምህራንና አመቻቾች የእርስ በርስ የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- የትምህርት ምዘናና የማጠቃለያ ፈተና በማዘጋጀት መስጠት፣
- የተማሪዎችን የትምህርት ውጤት የሚያሻሽሉ ፕሮግራሞችን በማቀድ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ እቅዶች፣ ፕሮግራሞችና የበጀት ዝግጅት ማስተባበር፣
- የሁሉንም ተማሪዎች ትምህርት፣ የሁሉንም ሰራተተኞች አስተዳደርና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው የፖሊሲ አፈጻጸም መቆጣጠር፣
- የሚጠበቁ ውጤቶችንና ግቦችን በማስቀመጥ ለአመቻቾች ተግባራትንና ኃላፊነቶችን ቆጥሮ በመስጠትና የሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም በመገምገም የመምራት፣የማስተዳደርና የማነቃቃት ተግባራትን ማከናወን፣
- የህብረተሰብ ተሳትፎን ለማሳደግ እንዲሁም የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የቀበሌው አስተዳደርና የጣቢያ አስዳደር ኮሚቴዎች የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያውን በባለቤትነት እንዲደግፉ ለማድረግ ከአካባቢው ማህበረሰብና ተሰሚነት ካላቸው ተጽእኖ ፈጣሪ ማህበረሰቦች ጋር በጋራ መስራት፣
- ሃገራዊና አካባቢያዊ ፖሊሲዎች እንዲሁም የትምህርት ቤት የደረጃ ምዘና ጥናት ውጤቶች ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች አተገባበርን ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፣ እንደአስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምት መውሰድ፣
- ለመማር ማስተማሩና ለክፍል ውስጥ የትምህርት አቀራረብና አመራር የሚያገለግሉ ፈጠራ የታከለባቸውን በቀላሉ ሊተገበሩ የሚችሉ ስልቶችን መቅረጽ፣
- ተገቢ የሀብት አጠቃቀም እንዲኖር በትጋት መስራት፣
- ጣቢያውን ለማስተዳደር (ከስታንዳርዱና የአተገባበር መመሪያው ስለሚወጡ አሰፈላጊ የሆኑ ህጎችና አሰራሮችን ማወቅና ለሌሎች ማሳወቅ ፣
- ከአመቻቾች፣ ከልዩ ልዩ ኮሚቴዎችና ማህበረሰቦች ጋር መልካም ግንኙነቶችን ማጎልበት።

### 4.2.7.የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ስትራቴጂክ ዓላማዎች ለማሳለጥ የሚያስችሉ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ረገድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በማስረጃ ላይ

የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጥራት ያለው የምርምር ስራ በመስራት ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አስተዋፅኦ በፍጥነት ይፈለጋል፡፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሚከተሉት ሊያግዝ በሚችል መልኩ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር በከፍተኛ ሁኔታ ይፈለጋል።

- ተገቢነት ያለው የአርብቶ አደር ስረዓተ ትምህርትና አዳዲስ የፈጠራና የችግር መፍቻ መፍትሂዎች ያሉት የጥናትና ምርምር ውጤት ማቅረብ፣
- የስትራቴጂ ዝግጅትንና ትግበራን ለማገዝ እንዲቻል ግብረ መልስና የምርምር ውጤቶችን ለክልል ትምህርት ቢሮዎችና ለትምህርት ሚኒስቴር ማቅረብ፣
- የሰው ሃይል አቅምን ለማልማት እንዲቻል የሚከተሉትን መንገዶች መጠቀም፡-
    - ክልል ትምህርት ቢሮዎችን በማመካከር፣ በማገዝና በቅርበት አብሮ በመስራት፣ የአቅም ክፍተቶችን በመለየት የትምህርት ባለሙያዎችን፣ ሱፐርቫይዘሮችን፣ የትምህርት ስራ አመራሮችን፣ የፈፃሚዎችንና የአጋሮችን አቅም የሚገነቡ ስልጠናዎችን መስጠት።
    - ለክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ ለዞን ትምህርት መምሪያዎችና ለወረዳ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤቶች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
    - የአርብቶ አደር ትምህርትን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣
    - ትምህርት ቢሮዎች የሚያደርጉትን ጥረት በማማከር፣ በመደገፍና በቅርብ አብሮ መስራት የአርብቶ አደር ትምህርት አቅርቦትን ማሻሻል፣
    - በአርብቶ አደር ትምህርት ላይ የውይይት ፎረሞችን ወርክሾፖችንና ሴሚናሮችን ማዘጋጀት፣
- በአርብቶ አደር አካባቢ ለሚሰሩ የትምህርት አጋር አካላት ሁሉ የሚጠቀሙበት የመረጃ ቋት በማዘጋጀት ልዩ ልዩ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን፣ የግምገማ ሪፖርትን፣ አህዛዊ መረጃዎችንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ።
- ለአርብቶ አደር ልጆች ልዩ የነፃ ትምህርት ዕድል ማመቻቸት፣
- ባለድርሻ አካላት የአርብቶ አደር ትምህርትን ሊያስፋፉ በሚችሉባቸው ሁኔታዎች ላይ፣ የውይይት ፎረሞችን፣ ወርክሾፖችንና ሴሚናሮችን ማዘጋጀት፣

### 4.2.8.የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች

በአርብቶ አደሮች አካባቢ ለሚሰሩ መምህራንና አመቻቾች ተገቢውን ትምህርት በማዘጋጀት መስጠት ሀገራዊና ክልላዊ ስትራቴጂያዊ እቅዶችን ለመተግበር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡ ፡

ስትራቴጂዎቹ ለትምህርት ጥራት አፅንኦት የመስጠት አስፈላጊነትን የሚጠቁሙ ሲሆን፣ በማስተማር ተግባር የተሰማሩ መምህራን ብቃታቸውን በየዕለቱ የሚያሻሽሉ መሆን አለባቸው። በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊዎች ይኖሯቸዋል።

- በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት በንቃት በመሳተፍ ስረዓተ ትምህርቱ የአርብቶ አደሮችን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። በተጨማሪም ወቅታዊ የስርአተ ትምህርት ክለሳና የመማሪያና የማስተማሪያመፅሀፍት ግምገማ በማድረግ ተስማሚ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና ማስተዋወቅ፣
- የመምህራን /አመቻቾች ዝግጅትን በሚከተሉት መንገዶች ማሻሻል፡-
    - የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣ የተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶች፣ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት፣ የተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርት መምህራንና አመቻቾች ውቅታዊ ስልጠና እንዲያገኙ ተቋማዊ አሰራር መፍጠር፣
    - የመምህራንና የአመቻቾችን ስልጠናዎች ከአርብቶ አደር የኑሮ ሁኔታ አንጻር መቃኘትና በየወቅቱ ማሻሻል፣
    - የአዲስ ምሩቅ መምህራንና አመቻቾችን የክፍል ውስጥ የማስተማር ተግባር አፈፃፀም በቦታው በመገኘት የሱፐርቪዥንና ግብረ መልስ ተግባር ማከናወን፣ ውጤቱንም ቀጣይ ለሚዘጋጁ የአጭርና የረጅም ጊዜ ሙያዊ የመምህራንና የሰራተኞች ልማት ስልጠና ፕሮግራም ዝግጅት እንደ ግብአት መጠቀም፣
    - በተከታታይ የስራ ላይ የስልጠና ፕሮግራሞች የአመቻቾችን የእውቀትና የሙያ ብቃት በመገንባት የትምህርት ዝግጅታቸውን ስታንዳርድ ማሳደግ።
- ከዩኒቨርሲቲዎችና ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በትብብር በመስራት ፍላጎትን ያማከለ የአርብቶ አደር ትምህርት የምርምር ስራ ማካሄድ።
- የርቀት ትምህርት አሰጣጥ ስርዓትን በመቅረጽ የመምህራንንና አመቻቾችን የሙያ ደረጃ ማሳደግ፣

### 4.2.9.ከአጋር ድርጅቶች የሚጠበቁ ተግባራት

- የሚስፈልገውን የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤
- ለክላስተር ሱፐርቫይዘሮች፣ ለርዕሳነ መምህራንና አመቻቾች ስልጠና መስጠት፣ የጣቢያ አመቻቾችን የትምህርት ደረጃ በማሳደግ ሂደት ላይ መሳተፍ፤
- የሙያና የልምድ ማካፈል አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።

- በአጋርነት ፎረም ስር ሆነው በክልሎች ቴክኒካል ኮሚቴ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ`፤
- በየደረጃው ካሉ የትምህርት ተቋማት ጋር በመመካከር የአርብቶ አደር ተማሪዎችና ማህበረሰብ የትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስልቶችን መቀየስ፣

# ክፍል አምስት፡

## ክትትል፣ ግምገማ እና የትምህርት መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ሥርዓት

### 5.1. የክትትልና ግምገማ ስርዓት

የስትራቴጂውን አተገባበርና አፈፃፀም እንዲሁም መሻሻልና ውጤታማነት ለመገምና መከታተል ክትትል ወሳኝ ነው። የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ዕቅድ ለማዘጋጀትና ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት ወቅቱን የጠበቀና አስተማማኝ መረጃ ያስፈልጋል። አሁን ያለው የመረጃ ፍሰት ችግርና ተቋማዊ የመረጃ አያያዝ ደካማ መሆን ውጤታማ የፖሊሲ አተገባበር እንዳይኖር፣ እንዲሁም በስርአቱ ላይ የአቅም ችግር በመፍጠር የአርብቶ አደር ልጆችን ፍላጎቶች ለመለየትና ለማሟላት የሚያስፈልገውን መረጃ ማግኘት አያስችልም።

ክፍተቶችን ለመለየት የሚጠቅሙ ጠንካራ ማስረጃዎችን በመጠቀም በአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለውን ስትራቴጂና የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈፃፀምን በፌደራል፣ በክልል፣

በወረዳ፣ በቀበሌ፣ በትምህርት ቤት እና በመማሪያ ማዕከላት ደረጃዎች ባለማቋረጥ ክትትልና ግምገማ ሊደረግ ይገባል። እነዚህን ክፍተቶች ለማጥበብ ግብረ መልስና የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት አቅም መገንባት ያስፈልጋል። የአፈፃፀም አመላካቾችን ግልጽ በማድረግ አመላካቾቹ ከስትራተጂያዊ ዓላማዎች አኳያ መሻሻል መኖሩን መለካት መቻላቸውን በማረጋገጥ መምራት ያስፈልጋል። አሁን በስራ ላይ ያለውን የመረጃ አደረጃጀት ስርዓት የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራተጂያዊ ዓላማዎችን ተፈጥሯዊ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው።

የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ በእያንዳንዱ የትምህርት አስተዳደራዊ መዋቅር ደረጃ የአመራሩን ፍላጎትና ተግባራትን ያገናዘ መሆን አለበት።በትምህርት ላይ የሚደረገውን ውይይት ለማሻሻል ብሔራዊና ክልላዊ የአርብቶ አደር የትምህርት ፎረም በማቋቋም በየተወሰነ የጊዜ ገደብ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይመከራል። እነዚህ ሪፖርቶች የትምህርት የመረጃ አያያዝና አደረጃጀት ስርዓት የሚደግፍና ስትራተጂዎችን ለመለወጥና በድጋሚ ለማስተካከል ሚና አላቸው።ለዚህም የሚከተሉት ተግባራት እንዲከናወኑ ይመከራል፡-

- በሁሉም ደረጃዎች የአፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ በማካሔድ አግባብነት ያለው ግብረ መልስ መስጠትና ፈጠራ፣ የቡድን ስራ ማበረታታትና በአርብቶ አደር ትምህርት ስትራተጂ ላይ የባለቤትነት መንፈስ በመፍጠር፣
- በትምህርት ውጤቶች ላይ የተመሰረቱ የመከታተያና የመመዝገቢያ ስነ ዘዴዎችን በመጠቀም ተሻሽሎ በስራ ላይ የዋለው ስትራተጂ ስኬታማ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ፣
- በትምህርት ስረዓቱ ውስጥ ውጤታማ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም የሁለትዮሽ የመረጃ ፍሰት ይኖር ዘንድ የሚና ግልፀኝነት ማሻሻል፣
- የአርብቶ አደር ትምህርት የውይይት ፎረሞችን በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ ማቋቋም፣
- ትምህርት ቤት አማራጭ የመሰረታዊ ትምህርት ላይ የተመሰረተ የስራ አመራርን በይበልጥ በማጠናከር፤ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ በተለይም ወላጆች በትምህርት ቤት / በመማሪያ ማዕከላት የሚደረጉትን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ያልተማከለ ስርዓቱን በይበልጥ ማስረፅ፣

- ያልተማከለ የትምህርት ስርዓቱን ይበልጥ በማስረጽ በትምህርት ቤቶች፣ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የአርብቶ አደር ማህበረሰብን፣ በተለይም የወላጆችን የትምህርት ስራ አመራር ተሳትፎ ማሻሻል፡፡
- የክትትልና ግምገማ ስራ እንዲያከናውኑ የተመደቡ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስራቸው በተሽከርካሪ እጥረት ምክኒያት እንዳይታወክ የትራንስፖርት ችግር መፍታት፣
- የትምህርት ቤት ማሻሻያ ዕቅዶችንና የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ስታንዳርዶችን በክልል ደረጃ በመቃኘት የአርብቶ አደር ትምህርት በእነዚህ ደረጃዎች መሰረት እየተተገበረ መሆኑን መለየት፡፡ በዚህም መሰረት ማንኛውም አስፈላጊ ማሻሻያ ተካቶ መተግባርና መገምገም አለበት፡፡

## 5.2. የትምህርት መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ስርዓት

- በሁሉም የአርብቶ አደር ትምህርት መዋቅሮች ጠንካራ የመረጃ አደረጃጀት ስርዓት በመመስረት የመረጃ አሰባሰቡ ወቅታዊ፣ ትክክለኛና አግባብነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣ የመልካም ተሞክሮዎችን ሰነዶን በመያዝ እንዲሁም የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና የዓመት ሪፖርቶች በወቅቱ ተዘጋጅተው እንዲሰራጩ ማድርግ፣
- አካባቢያዊ እቅዶች ትግበራዎች በመረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- ተጨማሪ ፍላጎቶችን ለመለየትና ተገቢ የሆኑ ምላሾችን መስጠት ይቻል ዘንድ ከቦታ ወደ ቦታ የሚደረግ ዝውውርንና የእንቅስቃሴውን መረብ መመርመር፣
- በየደረጃው ያሉ የትምህርት ባለድርሻ አካላት የአርብቶ አደር አካባዎችን የስራ ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ የትምህርት ስራ እንቅስቃሴዎችን መዝግቦ በመያዝ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ማካተት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የአርብቶ አደር ትምህርት የውይይት መድረኮች ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ከክልልና ከፌደራል በተውጣጡ ተሳታፊዎች በእቅዱ ላይ የተቀመጡ የትምህርት ስራዎችን አተገባበር በየሶስት ወሩ በመገምገም የጎላ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በተጨማሪም የአርብቶ አደር ትምህርት የውይይት ፎረሞችና ትምህርት ሚኒስቴር በየስድስት ወራቱ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የወረዳ፣ የክልልና የፌደራል ተሳታፊዎች በእቅዱ

ላይ የተቀመጡትን ስራዎች የአተገባበር ሂደት ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ አኳያ ይገመግማሉ፣ ልምድም ይለዋወጣሉ።

- በክልልና በብሄራዊ ደረጃዎች ዓመታዊ የትምህርት ኮንፈረንሶችን ማካሄድ
- ትምህርት ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአርብቶ አደር ትምህርት የውይይት መድረኮችን ጨምሮ ሌሎች መድረኮችን በመፍጠር ከአተባበር ሂደት የሚመነጩ ችግሮችን በመለየት በኮንፈረንሱ ላይ ለውይይት የሚቀርቡ ዝርዝር ጉዳዮችን አጀንዳ ያዘጋጃል።
- በሁሉም ደረጃዎች የአርብቶ አደር ትምህርትን በተመለከተ መደበኛና የተቀናጁ የክትትልና ግምገማ ስራዎችን ማከናወን የትምህርት ስትራቴጂውን አፈፃፀም ከመከታተልም በላይ የአርብቶ አደሮችን ትምህርት እድገት ለማፋጠን ትልቅ እገዛ ይኖረዋል።